Office of the
State Superintendent of Education

# የኮሎምቢያ አውራጃ

# የመጠበቂያዎች መመሪያ

# ማስታወቂያ

## የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ልጆች ወላጆች መብቶች

**በጃንዋሪ 2011 በድጋሚ የተከለሰ**

**መግቢያ**

810 First Street, NE, 9th floor, Washington, DC 20002
Phone: 202.727.6436 • Fax: 202.727.2019 • www.osse.dc.gov

## የኮሎምቢያ አውራጃ የመጠበቂያዎች መመሪያ ማስታወቂያ

## SPECIAL EDUCATION PROCEDURAL SAFEGUARDS REQUIREMENTS UNDER THE INDIVIDUALS WITH DISABILITIES EDUCATION ACT (IDEA)

### ጃንዋሪ 2011 በድጋሚ የተከለሰ

“አካል ጉዳት ተፈጥሮዋዊ የሆነ የሰው ልጅ የኑሮ ልምድ ነው እናም በምንም አይነት የሰዎችን በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን የተሳትፎ መብት የሚገድብ መሆን የለበትም። የአካል ጉዳት ያለባቸውን ልጆች የትምህርት ወጤቶች ማሻሻል እኩል ዕድል፣ ሙሉ ተስትፎ፣ ያለጥገኝነት መኖር፣ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ መድረግ የብሔራዊ ፖሊሲያችን ዋናው አካል ነው።” **መግቢያ ሃሳብ**

የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች የትመህርት ደምብ (IDEA)፣ የአካል ጉዳት ስላለባቸው ሰዎች የትምህርት የሚያውራው የፌደራል ህግ፣ ትመህርት ቤቶች ስለጥበቃ መመሪያዎች ማሰታወቂያ የተሟላ ማስታወቂያ ለወላጆች ማቅረብ አለባቸው። የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽህፈት ቤት (OSSE)፣ እንደ ግዛት የትምህርት ኤጀንሲ(SEA)፣ የእነዚህን የመመሪያ መጠቢቂያዎች እንዲያቀርብ ይጠብቅበታል።

የዚህ ማስታወቂያ ቅጂ በትመህርት ቤቶች በአመት አንድ ጊዜ ለወላጆች መሰጠትለ አለበት፣ በሚከተሉት ምክንያቶች ከሚሰጠው በተለየ፡-

- በመጀመሪያው ሬፍራል ወይም በእርስዎ ጥያቄ በሚደረግ ግምገማ፤
- በ 34 CFR §§300.151 ስር በ 300.153 መሰረት ቅሬታ ካቀረቡ ወይም በትመህርት አመቱ[1] ውስጥ በ 34 CFR §300.507 መሰረት እየተኪያሄደ ያለ የቅሬታ ሂደት ካለ ፤
- የምደባ ሁኔታውን ሊቀየር የሚችል የስነስርአት እርምጃ በልጅዎ ላይ ለመውሰድ ሲወሰን፤ <u>እና</u>
- በእርስዎ ጥያቄ።

ይህ ሰነድ የ IDEA [IDEA ክፍል B; PL 108-446; 20 USC § 1400 et seq.] አዲሶቹን ሃላፊነቶች እና የኦገስት ١4፣ 2006 የአፈጻጸም ደምቦች፣ እንዲሁም በዲሴምበር 3١፣ 2008 ተግባራዊ የሆኑ የፌደራል ደምቦች ላይ የተደረጉ ለውጦችን ያንጸባርቃል። ይህ ሰነድ የዩ.ኤስ የትምህርት ክፍል ሞዴል የመመሪያ ጥብቃዎች ማስታወቂያን የሚመለከት እና በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ መካተት ያለበትን የተለየ የኮሎምቢያ አውራጃ መስፈርቶችን ያካትታል።

<u>ይህንን ሰነድ የሚመለከቱ ጥያቄዎች ለሚከተለው ሊቀርቡ ይችላሉ</u>:
**Office of the State Superintendent of Education**
**Division of Special Education**
810 First Street NE, 5th Floor
Washington, DC 20002
(202) 741-0273

ይህ ሰነድ በኤሌክትሮኒክ በሚከተለው ላይ ይገኛል:
http://www.osse.dc.gov

[1] በ 34 CFR §§300.151 ስር 300.153 መሰረት እርስዎ የመጀመሪያውን ቅሬታ በሚያቀርቡበት ጊዜ ወይም በትምህርት አመቱ ውስጥ 34 CFR §300.507 መሰረት የቅሬታ ሂደት እየተኪያሄደ ከሆነ ትምህርት ቤቱ የደህንነት መመሪያ ቅጂውን ሊያቀርብልዎ ይገባል ሆኖም ግን ተከታታይ ቅሬታዎች ወይም በተመሳሳይ የትምህርት አመት ተከታታይነት ያላቸው የቅሬታ ሂደቶች የቀረቡ ከሆነ ይህ ተግባራዊ አይሆንም።

**ማውጫ**


**ክፍል ለ የመመሪያ ጥብቃዎች ማስታወቂያ ክለሳ........................................................................... 5**

**አጠቃላይ መረጃ ......................................................................................................... 5**

ሪፈራል የማነሳሳት ዕድልና የግምገማ አካሄዶች

የመጀመሪያ ግምገማ የጊዜ ሰሌዳ

ዳግም ግምገማ

በፅሁፍ የቀረበ ቅድመ ማሳወቂያ

በፅሁፍ የቀረበ ቅድመ ማሳወቂያ ይዘት

በሚረዱት ቋንቋ የሚወጡ ማስታወቂያዎች

የአፍ መፍቻ ቋንቋ

የኤሌክትሮንክ መልዕክት

የወላጆች ፈቃደኝነት ስምምነት

ገልለተኛ ትምህርትዊ ግምገማዎች

**የመረጃ ሚስጥራዊነት ......................................................................................... 11**

**ፍቺዎች**

ለወላጆች ማሳወቂያ

የማግኘት መብቶች

ሰነዶች ማግኘት

ከአንድ ልጅ በላይ ያሉ ሰነዶች

የመረጃ ዝርዝር ዓይነቶች እና የሚገኙበት ስፍራዎች

ክፍያዎች

በወላጆች ጥያቄ መሰረት ሰነዶችን ማሻሻል

የችሎት እድል

የችሎት አኪያሄዶች

የችሎት ውጤት

የግል ማንነተን ሊገልፁ የሚችሉ መረጃዎችን የመግለጽ ስምምነት

ጥበቃዎች

መረጃዎች የማስወገድ

**የአቤቱታ አካሄዶች ......................................................................................................... 15**

በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ መስሚያ እና በግዛት አቤቱታ አካሄዶች መካከል ያለ ልዩነት

የግዛት አቤቱታ አኪያሄዶች አቀባበል ..........................................................................................15

የግዛት ዝቅተኛ አቤቱታ አኪያሄዶች

የግዛት አቤቱታ ማስገባት

**በሂደት ላይ ያሉ አቤቱታ አኪያሄዶች ........ ..........................................................................17**

በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ማስገባት

በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ

ሞዴል ቅፆች

ድርድር

መፍትሄ መስጫ ሂደት

**በሂደት ላይ ያሉ አቤቱታዎች ችሎት ........................................................................................21**

ገለልተኛ በሂደት ላያ ያለ አቤቱታ መስሚያ ችሎት

የችሎት መብቶች

የችሎት ውሳኔዎች

**የይግባኝ ጥያቄዎች..................................................................................................................... 23**

የውሳኔዎች መጨረሻ፤ ይግባኝ

የችሎቶች የጊዜ ገደብ እና አመቺነት

ሲቪል እርምጃዎች፣ እርምጃዎቹን ለማስገባት የተሰጠውን የጊዜ ገደብ ጨምሮ

በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ እና ችሎቱ በሂደት ላይ እያለ የአንድ ልጅ ምደባ

የጠበቃ ክፍያዎች

**በአካል ጉዳተኛ ልጆች ላይ የዲሲፒሊን እርምጃ የመውሰድ አኪያሄዶች ..........................................................26**

የትምህርት ቤት ሰራተኞች ስልጣን

በዲሲፒሊን ግድፈት ምክንያት የመማሪያ ቦታ ለውጥ
የመማሪያ ቦታ ውሳኔ
ይግባኝ
የአቤቱታ ጊዜ መመሪያ
ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ገና ቡቁ ላልሆኑ ልጆች የሚደረጉ ጥበቃዎች
በህግ እና ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የሚደረጉ እርምጃዎች እና ሪፈራል

**በወላጆች ብቻ ልጆችን በህዝብ ገንዘብ ወደ ግል ትምህርት ቤቶች የማስገቢያ መስፈርቶች ..................................31**
አጠቃላይ

## **ክለሳ፡ ክፍል ለ** *የመመሪያ ጥብቃዎች ማስታወቂያ*



*እንደወላጅ፣ ለእያንዳንዱ የልዩ ትምህርት ሂደት የአካሄድ ጥበቃዎች ተብሎ የሚታወቁ መብቶች አልዎት። የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆች በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም* (Individualized Education Program (IEP)) *ስር ገለልተኛ እና ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት* (free appropriate public education (FAPE)) *ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የተነደፈ ፕሮግራም ተዘጋጅቶላቸዋል።*

*ይህ ሰነድ እንደጥበቃ አኪያሄድ ማስታወቂያ ያገለግልዎታል እንዲሁም ልዩ ትምህርትን በተመለከተ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ትምህርት አዋጅ እና የኮሎምቢያ አውራጃ ስር ያሉትን ህግጋትን እንዲሁም የልጅዎን እና የእርስዎን የተለዩ መብቶች ለመረዳት ያግዝዎታል፡፡ የእነዚህ የጥበቃዎች አኪያሄድ ሙሉ ጽሁፍ በፌደራል ቁጥጥሮች ኮድ አርእስት 34፣ ክፍል 300፣ አርእስት 38፣ የኮሎምቢያ አውራጃ ኮድ ምዕራፍ 25ለ፣ እና አርእስት 5፣ ንኡስ አርእስት ሰ፣ የኮሎምቢያ አውራጃ መዘጋጃ ቤት ደምቦች* (5ሰ DCMR) *ምዕራፍ 30 ውስጥ ይገኛል።*

*ይህ የጥበቃ ማስታወቂያ በ* §300.148 (*ልጁ በህዝብ ወጪ የግል ትምህርት ቤት ውስጥ እስኪማር ድረስ*)፣ §§300.151 *በ* 300.153 *ውስጥ* (*የግዛት አቤቱታ አኪያሄድ*)፣ §300.300 (*የወላጅ ስምምነት*)፣ §§300.502 *እና* 300.503 (IEP *እና ቅደሚያ የጽሁፍ ስምምነት*)፣ §§300.505 *በ* 300.518 *ውስጥ* (*ሌሎች የጥበቃዎች አኪያሄዶች፣ ለምሳሌ፣ ግልግል፣ የቅሬት አኪያሄድ፣ የአፈታት ሂደት፣ እና ገለልተኛ ሂደት ችሎቶች*)፣ §§300.530 *በ* 300.536 *ውስጥ* (*የጥበቃዎች አኪያሄድ የክፍል ለ ደምቦች አካል በሆነው ንዑስ ክፍል መ*)፣ *እና* §§300.610 *በ* 300.625 *ውስጥ* (*በንዑስ ክፍል ረ ውስጥ የመረጃ አቀርቦት ሚስጥራዊነት*) *ስር የሚገኙትን የጥበቃዎች አኪያሄድ ማብራሪያ ያካተተ ነው።*

*በዚህ መመሪያ ስር የቀረበው መረጃ ላይ ማንኛውም ጥያቄ ካልዎት እባክዎ የእርስዎን አካባቢ ትምህርት ቤት፣ የእርስዎን አካባቢ አውራጃ ትምህርት ቤት፣ በተጨማሪ የአካባቢ የትመህርት ኤጀንሲ* (local education agency (LEA)) *ተብሎ የሚታወቀውን፣ ወይም የአውራጃ አካባቢ ትምህርት ቁጥጥር ጽህፈት ቤት* (Office of the State Superintendent of Education (OSSE))፣ *በኮሎምቢያ አውራጃ የግዛት ትምህርት ኤጀንሲን* (State Education Agency (SEA)) *ያነጋግሩ።*

**[ማስታወቂያ፡ ልጅዎ የሚማርበት LEA በ LEA ስር የሚማሩ ተማሪዎች ላይ ተግባራዊ የሚሆን ተጨማሪ የጥበቃ አኪያሄድ ሊኖረው ይችላል። የእርስዎ LEA ይህንን መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት። ይህንን ስለመሳሰሉ ተጨማሪ የጥበቃዎች መረጃ ለማግኘት የእርስዎን አካባቢ LEA ያነጋግሩ ይችላሉ።]**

## አጠቃላይ መረጃ

### ሪፈራልን የማነሳሳት እድል እና የግምገማ አካሄዶች

#### 34 CFR §§300.301, 300.304፣ እና 300.305; D.C. ይፋዊ ኮድ § 38-2561.02; 5E DCMR § 5-3004

*ግምገማ የአካሄዶችን ስብስብ የያዘ ሂደት ነው እና/ወይም በ*IDEA *እና በኮሎምቢያ አውራጃ ህግ መሰረት የሚደረግ አሰሳ ሲሆን የሚከተሉትን ለመወሰን ይከናወናል፡-* (1) *አንድ ልጅ አካል ጉዳተኝነት እንዳለው/ት እና እንደሌለው/ላት ለማወቅ፣ እና ካለው/ት*(2) *የልዩ ትምህርት የተፈጥሮ ሁኔታ እና ስፋት እንዲሁም ደግሞ ልጁ/ቷ የሚያስፈልጋቸው ተዛማጅ አገልግሎቶች። ልጅዎ አካል ጉዳተኛ እንደሆነ/ች ለመገመት* LEA *ወይም እርስዎ ግምገማ ይደረግለት/ላት ዘንድ መጠየቅ አለባችሁ።*

*ግምገማው በሚካሄድ ጊዜ፣ ስለ ልጁ/ቷ ተዛማጅ የሆኑ በትክክል የሚታዩ፣ በእድገት ላይ ያሉ እና አካዳሚክ መረጃዎችን፣ ከወላጅ የሚሰጡ መረጃዎችን ጨምሮ* LEA *የተለያዩ የአሰሳ መሳሪያዎችን እና ዘዴዎችንመጠቀም ይገባዋል። በተጨማሪም፣ ልጅዎ አካል ጉዳተኝነት አለበት/ባት ብሎ ለመገመት እና አግባብ ያለውን የትምህርት ፕሮግራም ለመመደብ* LEA *አንድ የመለኪያ ወይም የአሰሳ መስፈርትን እንደ ዋና የመመዘኛ መስፈርት መጠቀም አይገባውም።* LEA *በቴክኒኩ ረገድ በግንዛቤያዊ እና ባህሪያዊ እንዲሁም ደግሞ አካላዊ እና በእድገት ላይ ተፅእኖ የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን አንፃራዊ አስተዋፅኦዎችን የሚገመግሙ ፍፁም መሳሪያዎችን መጠቀም አለበት።*

*እያንዳንዱ* LEA *አሰሳዊቹ ተመርጠው በተግባር ላይ እንደዋሉ ማረጋገጥ ይገባዋል ስለዚህም በዘር ወይም በባህል ላይ መሰረት ያደረገ መድልዎ አይኖርም። ከዚህ በተጨማሪም፣ ሁሉም አሰሳዎች በልጅዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ነው መከናወን ያለባቸው። በልጅዎ የግምገማ ሁኔታ ላይ መሰረት ያደረገ ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ይህም ልጅዎ በመደበኛነት በቤት ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት አካባቢ የሚጠቀመው/የምትጠቀመው ቋንቋ ማለት ነው* (*በሁለታችሁ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መካከል ልዩነት ካለ የእርስዎን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለማለት አይደለም*)።

*ግምገማው መካሄድ ያለበት በሰለጠነ እና እውቀቱ ባለው ባለሞያ በአሰሳው ሂደት ውስጥ በተቀመጡት ትዕዛዛት ላይ መሰረት በማድርግ መሆን ይገባዋል፣ እንዲሁም አሰሳው በስራ ላይ የዋለው ትክክለኛ እና ተአማኒ ውጤት ለማግኘት አላማ መሆን አለበት።*

ለግምገማ የሚውሉ ተጨማሪ አካሄዶች እንደሚከተሉት ይሆናሉ፡-

LEA አሰሳዎቹ የተወሰኑ የትምህርት ፍላጎቶች ሁኔታዎችን ለመገምገም የታለሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት እንዲሁም ደግሞ የልጅዎን አይኪው(IQ) ለመመዘን የተነደፉ መሆን የለባቸውም፤

- የLEA አሰሳዎች የልጅዎን አቋም ወይም የውጤት ደረጃ ወይም ሙከራው ለመመዘን ያቀደውን ሌሎች ሁኔታዎችን እንዲሁም ልጅዎ ባለው/ላት በሴንሰሪ፣ በእጅ የሚከናወኑ ተግባራት፣ ወይም በንግግር ክህሎት ላይ በተሻለ እና ትክክለኛ ውጤትን በሚያንፀባረቅ መልኩ አሰሳዎቹ እንደተመረጡ እና በተግባር ላይ እንደዋሉ ማረጋገጥ ይገባዋል፤
- የLEA ልጅዎ አካል ጉዳተኝነት ይኖርበታል/ባታል ተብሎ በተጠረጠረባቸው/ ችባቸው አካባቢዎች ሁሉ ሙከራ እንደተደረገለት/ላት ማረጋገጥ አለበት፤
- ልጅዎ በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ ከአንድ LEA ወደ ሌላ ከተዛወረ/ች፣ ሁለቱም LEAዎች የአሰሳውን በፍጥነት መጠናቀቅ ለማረጋገጥ እንደ አስፈላጊነቱ እና በተቻለ ፍጥነት ማስተባበር ይገባቸዋል፤
- የልጅዎን ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ የአገልግሎቶች ፍላጎቶችን ለይቶ ለማወቅ ግምገማው በበቂ ሁኔታ ሁሉን ያካተተ መሆን እንደሚገባው LEA ማረጋገጥ አለበት፤ እና
- የልጅዎን የትምህርት ፍላጎቶችን የሚወስኑ ግለሰቦች ተዛማጅ መረጃዎችን የሚያቀርቡ የአሰሳ መሳሪያዎች እና ዘዴዎች እንደተሰጣቸው LEA ማረጋገጥ ይገባዋል።

### የመጀመሪያ ግምገማ የጊዜ ሰሌዳ

በኮሎምቢያ አውራጃ ህግ ስር፣ አካል ጉዳተንነት ይኖረዋል/ታል ተብሎ የሚገመትን/የምትገመትን ልጅ የመጀመሪያ ግምገማ ብቁነት ጨምሮ LEA ማጠናቀቅ ይገባዋል፣ ይህም በፅሁፍ የቀረበውን ሪፈራል በደረሰ  በመቶ ሃያ (120) የቀን መቁጠሪያ  ቀናት ውስጥ መሆን አለበት። ሆኖም ግን፣ የአንድ መቶ ሃያ (120)  ቀን የጊዜ ገደቡ የሚከተሉት የሚከሰቱ ከሆነ በLEA ላይ በስራ ላይ አይውልም፡-

- እርስዎ በተደጋጋሚ ልጅዎን ለግምገማ አዘጋጅተው ካላመጡ ወይም ፈቃደኛ ካልሆኑ፤
- ለግምገማ መስማማትዎን  የሚገልፁ ጥያቄዎችን ካልመለሱ ወይም ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆኑ፤ ወይም
- የ120 ቀኑ የጊዜ ገደብ ከተጀመረ በኋላ ልጅዎን በሌላ የLEA ትምህርት ቤት አስመዝግበውት ከነበረ፣ ሆኖም ግን የቀድሞው LEA ልጅዎ አካል ጉዳተኛ እንደሆነ/ች እና እንዳልሆነ/ች ከመወሰኑ በፊት። እነኝህ ልዩ ሁኔታዎች በተግባር ላይ የሚውሉት የሚከተሉት ካጋጠሙ ብቻ ነው፡-
    - አዲሱ LEA ግምገማውን በፍጥነት ለማጠናቀቅ በቂ የሆነ እድገትን እያሳየ ከሆነ፣ <u>እና</u>
    - እርስዎ እና አዲሱ LEA ግምገማው የሚጠናቀቅበትን ጊዜ ወስናችሁ ስምምነት ላይ ከደረሳችሁ ነው።

### ዳግም ግምገማ

ዳግም ግምገማ የሚተነተነው፣ ከመጀመሪያው የግምገማ ሂደት በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ የሚደረግ ግምገማ በማለት ነው፣ ይህም አካል ጉዳተኝነት ያለበት/ባት ልጅ አካል ጉዳተኛ እንዳለው/ላት በአግባቡ ለመገመት ነው። የዳግም ግምገማ አላማ እንደሚከተለው ይሆናል ፡-

- የልጁን/ቷን አሁን ያለውን የአካዳሚክ ውጤት እና ተዛማጅ የእድገት ፍላጎቶች ለመለየት፤
- ልጁ/ቷ ልዩ የትምህርት እና ተዛማጅ ፍላጎቶች በቀጣይነት ያስፈልገው/ጋት እንደሆነ ለመገምገም፤ <u>እና</u>
- የሚያስፈልገው/ጋት ከሆነ፣ በአገልግሎቶቹ ላይ ማንኛውም አይነት ጭማሪዎች ወይም ማሻሻያዎች ያስፈልጉ እንደሆነ ለመወሰን።

እርስዎ እና LEA ዳግም ግምገማ አስፈላጊ አይደለም ብላችሁ ካልወሰናችሁ በስተቀር፣ የልጅዎ ፍላጎቶች እንደተቀየሩ እና እንዳልተቀየሩ ለማወቅ፣ ዳግም ግምገማ ቢያንስ በሶስት ዓመት አንድ ጊዜ መከናወን አለበት። ሁኔታዎች ካስገደዱ ወይም እርስዎ እና የልጅዎ አስተማሪ ዳግም ግምገማ እንዲከናወን ከጠየቃችሁ፣ ዳግም ግምገማዎች በጣም በተደጋጋሚ ሊከናወኑ ይችላሉ። እርስዎ እና LEA ካልተስማማችሁ በስተቀር፣ ዳግም በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ መከናወን የለበትም።

## በፅሁፍ የቀረበ ቅድመ ማሳወቂያ

## 34 CFR §300.503 እና 5E DCMR §3025.1

የእርስዎ LEA በፅሁፍ የቀረበ ማሳወቂያ ሊሰጥዎት ይገባል (የተወሰነ መረጃ በፅሁፍ ይሰጥዎታል)፣ የሚከተለው ከመሆኑ በቂ ጊዜ በፊት፡-

- የልጅዎን መለያ፣ ግምገማ ወይም የትምህርት ምደባ፣ አልያም ደግሞ ለልጅዎ የFAPE አሰጣጥ፤ <u>ወይም</u>

- መለያን፣ ግምገማን ወይም የትምህርት ምደባ ወይም ለልጅዎ የFAPE አሰጣጥን ለማነሳሳት ወይም ለመለወጥ ፈቃደኛ አለመሆን።

**በፅሁፍ የቀረበ ቅድመ ማሳወቂያ ይዘት**

በፅሁፍ የቀረበ ቅድመ ማሳወቂያ የሚከተሉን ማካተት ይገባለዋል፡-

- LEA የጠየቀውን ወይም ለመውሰድ ፈቃደኛ ያልሆነበትን እርምጃ ያብራራል፤
- LEA ለምን እየጠየቀ እንደሆነ፣ ወይም እርምጃውን ለመውሰድ ለምን ፈቃደኛ እንዳልሆነ ያብራራል፤
- እያንዳንዱን የግምገማ አካሄድ፣ አሰሳ፣ ሰነድ፣ ወይም እርምጃውን ለመጠየቅ ወይም ላለመቀበል ውሳኔ የተደረገበትን በአገልግሎት ላይ የዋለውን LEA ሪፓርት ማብራራት፤
- በመጠበቂያዎች አካሄድ (procedural safeguards) አቅርቦቶች ስር በIDEA ክፍል B ውስጥ ያለዎትን የጥበቃዎች መግለጫ ያካቱ፤

- የዚህን የመጠበቂያዎች አካሄድ (procedural safeguards) ቅጅ በሚያገኙበት መንገድ መረጃን ይስጡ፤
- በIDEA ክፍል B ስር የአካሄድ ጥበቃዎች (procedural safeguards) እንዳለዎ ይነገርዎታል፣ እና በእርስዎ ውሳኔ የመስጠት መብት፣ የዚህን ጥበቃዎችን የሚያብራራውን የመጠበቂያዎች አካሄድ (procedural safeguards) ቅጂ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይነግርዎታል (LEA የሚጠይቀው ወይም ለመውሰድ ፈቃደኛ ያልሆነው እርምጃ ለግምገማ የመጀመሪያ ሪፈራል ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ ሁኔታ LEA የመጠበቂያዎች አካሄድ (procedural safeguards) ማሳወቂያን ቅጂ ለእርስዎ መስጠት ይገባዋል)፤

- የIDEA ክፍል Bን ለመረዳት ለእገዛ የሚደርሱባቸውን ምንጮች ያካቱ፤

- LEA ከግምት ውስጥ የሚያስገባቸውን ማንኛውንም አይነት አማራጮችን፣ እና እነኛ አማራጮች የታገዱበትን ምግንያቶች ያብራሩ፤ እና

- LEA ለምን እርምጃውን እንደጠየቀ እና እንደከለከለ የሚገልጹ ሌሎች ምክንያቶች ዝርዝርን ይስጡ።

**በሚረዱት ቋንቋ የሚወጡ ማስታወቂያዎች**

ማስታወቂያው የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

- ለአጠቃላይ ለህዝቡ ግልፅ በሆነ ቋንቋ የተፃፈ መሆን አለበት፣ እና

- በአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም በሌሎች እርስዎ በሚጠቀሙት መግባቢያ የቀረበ፣ ግልፅ ካልሆነ ለማከናወን የሚቻል አይደለም። o.

የአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም ሌሎች የመግባቢያ ዘዴዎች በፅሁፍ የሚቀርብ ከሆነ፣ LEA የሚከተሉትን ማረጋገጥ ይገባዋል፡-

- ማስታወቂያው ለእርስዎ በቃል መተርጎም አለበት፣ ወይም ለእርስዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም በሌላ የመግባቢያ ዘዴ ለእርስዎ መቅረብ አለበት፤

- እርስዎ የማስታወቂያውን ይዘት ተረድተዋል፤ እና
- እነኝህ ሁለቱ መስፈርቶች እንደተጣጣሙ በፅሁፍ የቀረበ ማረጋገጫ አለ።

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ**

**34 CFR §300.29**

*የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣* ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ያለው ሰው በሚኖር ጊዜ በአገልግሎት ላይ ይውላል፣ ይህ ማለት የሚከተለው ነው፡-

- በዚያ ሰው በመደበኛነት በአገልግሎት ላይ የሚውል ቋንቋ፣ ወይም በልጅ አንፃር ስናየው፣ በልጁ/ቷ ወላጆች በመደበኛነት በአገልግሎት ላይ የሚውል ቋንቋ፤ እና

- ከልጁ/ቷ ጋር በሚኖር በሁሉም የቀጥታ ግንኙነቶች (የልጁን/ቷን ግምገማ ጨምሮ)፣ በቤት ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት በመደበኛነት ልጁ/ቷ የሚጠቀምበት/የምትጠቀምበት ቋንቋ፣ መስማት ወይም ማየት ለተሳናቸው ሰዎች፣ ወይም ምንም የፅሁፍ ቋንቋ ለሌለው ሰው፣ የመግባቢያ ዘዴው በመደበኛነት ሰውየው የሚጠቀመው ቋንቋ ይሆናል (እንደ የምልክት ቋንቋ፣ ብሬል፣ ወይም የቃል ንግግሮች)።

## ኤሌክትሮኒክ መልዕክት

## 34 CFR §300.505

LEA ለወላጆች በኢሜይል ሰነዶችን እንደሚቀበል አማራጮችን ከሰጠ፣ የሚከተሉትን በኢሜይል ለመቀበል መምረጥ ይችላሉ:-

- በፅሁፍ የቀረበ የቅድመ ማሳወቂያ፤
- የአካሄዶች መጠበቂያ ማሳወቂያ፤ እና
- በሂደት ውስጥ ካለ አቤቱታ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ማሳወቂያዎች ።

## የወላጆች የፈቃደኝነት ስምምነት

## 34 CFR §§300.9 እና 300.300, እና 5E DCMR §3026.1

### ወላጆች የሚለው ቃል ፍቺ(34 CFR §300.30 እና 5E DCMR §3001.1)

«ወላጅ» የሚለው ቃል ፍቺ እንደሚከተለው ይተረጎማል (ሀ) ባዮሎጂካል ወይመ በጉዲፈቻ የሚያሳድግ ወላጅ፤ (ለ) የማደጎ ወላጅ (ሆኖም ግን ልጁን በመወከል የትምህርት ውሳኔን የማሳለፍ ስልጣኑ የባዮሎጂካል ወይም የጉዲፈቻ ወላጆች ሲሆን ይህ በስራ ላይ በዋለው ህግ ተለይቶ ይታወቃል፤ እና አሳዳጊው ወላጅ፣ የሚቀጥል፣ ከልጁ ጋር የረዥም ጊዜ የወላጅነት ግንኙነት ይኖረዋል፣ እንደ አስፈላጊነቱ በ IDEA ስር ትምህርታዊ ውሳኔውችን ለመውሰድ ፈቃደኛ ነው፣ እና ከልጁ ጋር የሚቃረን ፍላጎት የለውም)፤ (ሐ) አሳዳጊ በአጠቃላይ ለልጁ/ቷ እንደ ወላጅ እንዲያድጉ ፈቃድ የተሰጣቸው ወይም ለልጁ/ቷ የትምህርት ውሳኔዎችን እንዲያሳልፉ ፈቃድ ያላቸው ማለት ነው፤ (መ) በባዮሎጂካል ወይም ጉዲፈቻ ወላጅ ምትክ (እንደ አያቶች፣ የእንጀራ እናት/አባት ወይም ሌሎች ዘመዶች) ልጁ/ቷ አብረአቸው የሚኖሩ ግለሰቦች ወይም (ለልጁ/ቷ የድጋፍ ጥቅማጥቅም ህጋዊ በሆነ መልኩ ሃላፊነት ያለበት ግለሰብ)፤ ወይም (ሠ) በIDEA እና በኮሎምቢያ አውራጃ ህግ መሰረት የተሾመ የትምህርት ተወካይ። ልጁ/ቷ በኮሎምቢያ አውራጃ ህጋዊ ከለላ ስር ከሆነ ይህ ውል የኮሎምቢያ አውራጃን አያካትትም።

### የስምምነት ፍቺ

*ስምምነት ማለት:*

- መስማማትዎን ስለገለጹባቸው እርምጃዎች ሁሉም መረጃዎች ሙሉ በሙሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም በሌላ የግንኙነት አይነት (ለምሳሌ የምልክት ቋንቋ፣ ብሬል፣ወይም በቃል/አፋዊ ግንኙነት) ተገልጾሎታል፤
- ሰለእንዚያ እርምጃዎች ተረደተው እንዲሁም በጽሁፍ ተስማምተዋል፣ እናም ስምምነትዎ የእነዚያን እርምጃዎች ይገልጻል እንዲሁም የሚወጡትን ምዝገባዎች እና ለማን እንደሚሰጡ ይዘረዝራል (ካለ)፤ እና
- ስምምነትዎ በእርስዎ በኩል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን እና በማንኛውም ጊዜ ከስምምነቱ መውጣት እንደሚችሉ ተረድተዋል።

ልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ማግኘት ከጀመረ በኋላ ስምምነቱን መሰረዝ ከፈለጉ በጽሁፍ መሰረዝ አለብዎ። የእርሰዎ ከስምምነቱ መውጣት ስምምነትዎን ከሰጡ በኋላ ሆኖም ግን ከምዎጣትዎ በፊት የተወሰዱ እርምጃዎችን አይጻረርም (እንዳይፈጸሙ) አያደርግም። በተጨማሪም፣ እርስዎ ከስምምነት ከወጡ በኋላ LEA ልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ሰላማግኘቱ የተጠቀሱትን የልጅዎን የትምህርት መዝገቦች ማሻሻል (መለወጥ) አያስፈልገውም።

### ለመነሻ ግምገማ የወላጅ ስምምነት

በመጀመሪያ የሚከተሉት ሳይሟሉ በፊት LEA ልጅዎ በ IDEA በክፍል ለ መሰረት ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ለማግኘት በቂ ስለመሆኑ ለመወሰን የመነሻ ግምምገማ ማድረግ አይችልም፡

- ሰለቀረበው እርምጃ ቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ ሳያቀርብ፣ እና
- ቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ እና የወላጅ ስምምነት በሚለወ አርእስት ስር እንደተገለጸው የእርስዎን ስምነነት ሳያገኝ።

ልጅዎ አካል ጉዳተኛ እንደሆነ ለመወሰን የመነሻ ግምገማውን ለማድረግ LEA የእርሰዎን ገለጻ የተደረገበት ስምምነት ለማግኘት ተገቢ የሆነ ጥረት ማድረግ አለበት። የመነሻ ግምገማ እንዲደረግ ተስማሙ ማለት LEA ለልጅዎ ልዩ ትምህረት እና ተዛማጅ አገልግለቶች ማቅረብ እንዲጀምር ተስማሙ ማለት አይድለም።

ከመነሻ ግምገማው ጋር የተያያዘ አንድ አገልግሎት ወይም እንቅስቃሴ አለመስማማትዎን መሰረት በማድረግ LEA እርስዎን ወይም ልጅዎን ሌላ አገልግሎትን፣ ጥቅም፣ ወይም እንቅስቃሴ ሌላ የከፍል ለ መሰፈረት የሚያግደው እስካልሆነ ድረስ ከማቅረብ ሊያግድዎ አይገባም

ልጅዎ በህዝብ ትምህርት ቤት የሚማር ከሆነ ወይም ልጅዎን በህዝብ ትምህርት ቤት ማስተማር የሚፈልጉ ከሆነ እና ለመነሻ ግምገማው ስምምነት ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ ወይም ለስምምነት ጥያቄው ምለሽ ለመስጠት ከተሳንዎት፣ LEA የኮሎምቢያ አውራጃ የ IDEA ግልገል ወይም የቅሬታ ሂደት፣ የመፍቻ ስብሰባዎች፣ እና ገለልተኛ የሆነ የችሎት አኪያሄድን በመጠቀም ለልጅዎ የመነሻ ግምገማዎን ላማድረግ ሊፈልግ ይችላል፣ ሆኖም ግን አይገደድም። LEA ልጅዎን የማመላከት፣ የመለየት እንዲሁም የመገምገም ሃላፊነቱን አይተላለፍም፣ በእነዚህ ሁኔታዎች የልጅዎን ግምገማ ካለኪያሄደ በስተቀር።

**የተለዩ ደምቦች ስለግዛት ህጋዊ ከለላ የመነሻ ግምገማ**

*የግዛት ህጋዊ ከለላ፣* በ IDEA ጥቅም ላይ እንደዋለው ልጁን፣ በግዛት እንደተለየው ልጁ የሚኖርበትን ቦታ ያመለክታል፡

- የጉዲፈቻ ልጅ፤
- በግዛት ህግ ስር ያለ የግዛት ህጋዊ ከለላ፣ <u>**ወይም**</u>
- በህዝብ የህጻናት በጎ አድራጎት ኤጀንሲ ስር ያለ።

ማወቅ የሚገባዎ አንድ የተለየ ነገር አለ። ይህ መግለጫ የጉዲፈቻ ወላጅ ያሏቸውን የጉዲፈቻ ልጆችን በ IDEA እና በኮሎምቢያ አውራጃ ህግ ላይ የተገለጸውን የወላጅ ፊቺ የሚያሟሉ የጉዲፈቻ ወላጆችን አያካትትም።

ልጁ/ቷ በግዛት ህጋዊ ከለላ ስር ከሆነ/ች እና ከቤተሰቡ/ቧ ጋር የማይኖር ከሆነ እና የሚከተሉት ከተፈጸሙ፣ ልጁ/ቷ የአካል ጉዳት እንደለበት/እንደላባት ለመለየት የመነሻ ግምገማዎን ለማድረግ ስምምነት ከወላጆች ማግኘት:

- LEA የልጁን ወላጅ ለማግኘት ተገቢ የሆነ ጥረት ቢያድረግም የልጁን ወላጅ ማግኘት ካልተቻለ፤
- በግዛት ህጉ መሰረት የወላጆች መብት የተቋረጠ ከሆነ፣ <u>ወይም</u>
- ሰለትመህርት ሁኔታ ወሳኔ እንዲያሰልፍ ፍርድ ቤት ከወላጆች ሌላ ለሆነ ሰው መብት ከሰጠ እና ይህ ሰው ለመነሻ ግምገማው ከተስማማ።

**ለአገልግሎቶች የወላጅ ስምምነት**

የእርስዎ LEA ለልጅዎ ልዩ ትመህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከማቅረቡ በፊት እና የልጆዎ አቀማማጥ ላይ ለመለወጥ ከመወሰኑ በፊት መረጃ የተሰጠበት ስምምነት ከእርሰዎ ማግኘት አለበት።

LEA ለልጅዎ ልዩ ትመህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከማቅረቡ በፊት የእርስዎን መረጃ የተሰጠበት ስምምነት ለማግኘት ተገቢ ጥረት ማድረግ አለበት።

ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ/እንድታገኝ ስምምነትዎን ለመስጠት ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ካልሰጡ፣ ወይም እንዲህ ያለውን ስምምነት ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ አልያም ቆይተው ስምምነትዎን በፅሁፍ ካነሱ (ከሰረዙ)፣ የእርስዎ LEA የአካሄድ መጠበቂያዎችን (procedural safeguards) የአካሄድ መጠበቂያዎችን <u>ላይጠቀሙ</u> ይችላሉ (ይህ ማለት፣ ማደራደር፣ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ፣ የመፍትሄ መስጫ ስብሰባ፣ ወይም በሂደት ላይ ያለ ክፊል ችሎት) ስምምነት ላይ ለመድረስ ወይም ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች (በእርስዎ የIEP ቡድን የተመከሩ) ከእርስዎ ስምምነት ውጭ ለልጅዎ ሊሰጥ ይችላል።

ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ትምህርት እና ተዘማጅ አገልግሎትን እንዲያገኝ/እንድታገኝ ስምምነትዎን ለመግለጽ ፈቃደኛ ካልሆኑ፤ ወይም እንዲህ ያለውን ስምምነት ለመስጠት ጥያቄ ካልመለሱ፣ ወይም ፈቃድ ሰጥተዎ ከነበረ እና ቆይተው ደግሞ ፈቃዱን በፅሁፍ ካነሱ (ከሰረዙ)፤ የእርስዎ LEA የእርስዎን ስምምነት የሚጠይቀውን  ልዩ ትምህርትን እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለልጅዎ አይሰጥም፡-

- ለልጅዎ አግባብ ያለው ገለልተኛ የህዝብ ትምህርት (FAPE) ለማቅረብ በመስፈርቶች ጥሰት ላይ አይደለም፣ እነኝህን አገልግሎቶች ለልጅዎ ለማቅረብ እንደተሳነው፤ <u>እና</u>
- የግለሰብ ትምህርት ፐሮግራም (IEP) ስብሰባ ሊኖረው አያስፈልግም ወይም የእርስዎ ስምምነት ለሚጠየቅበት የእርስዎ ልጅ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች IEP መስራት አያስፈልግም።

ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ካገኘ/ች በኋላ ስምምነትዎን በማንኛውም ሰዓት በፅሁፍ ካነሱ (ከሰረዙ)፣ LEA አገልግሎቶቹን መስጠቱን ማቆም አለበት፣ ሆኖም ግን እነኛን አገልግሎቶች ለማቋረጥ ***በፅሁፍ የቀረበ የቅድመ ማሳወቂያ*** ርዕስ ስር እንደተብራራው ለእርስዎ በፅሁፍ የቀረበ የቅድመ ማሳወቂያ መስጠት አለበት።

***ለዳግም ምርመራ የወላጆች ስምምነት***

የእርስዎ LEA ልጅዎን ዳግም ከመገምገሙ በፊት፣ LEA ቀድሞውኑ አከናውኖት ካልነበረ በቀር፣ የእርስዎን ቅድሞ የተነገረ ስምምነት ሊኖረው ይገባል፡-

- ለልጅዎ ዳግም ግምገማ የእርስዎን ስምምነት ለማግኘት ምክንያታዊ የሆኑ ደረጃዎችን መውሰድ አለባቸው፤ <u>እና</u>
- እርስዎ ምላሽ አልሰጡም።

ለልጅዎ ዳግም ግምገማ ስምምነት ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ፣ ለልጅዎ ግምገማ የእርስዎን ፈቃደኛ አለመሆን የሚጥስ ውሳኔን ለመጠየቅ LEA ፣ የልጁን/ቷን ግምገማ ድርድርን፣ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታን ፣ የመፍትሄ መስጫ ስብሰባን፣ እና ገለልተኛ የአቤቱታ መስሚያ ችሎትን በመጠቀም አይሞክርም። ለመጀመሪያዎቹ ግምገማዎች፣ እንደ እርስዎ የመጀመሪያ ግምገማ LEA በዚህ አካሄድ ዳግም ግምገማውን መቀጠሉን ካቆመ በIDEA ክፍል B ስር ያለውን ግዴታዎች አይጥስም።

***የወላጅ ስምምነትን ለማግኘት ምክንያታዊ የሆኑ ጥረቶች ሰነዶችን ማሰባሰብ***

ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመስጠት፣ ልጅዎን ዳግም ለመገምገም፣ እና በግዛት ህግ ከለላ ስር ያሉ ልጆች ወላጆችን ለመጀመሪያ ግምገማ ለማግኘት፣ የእርስዎን ስምምነተ ለማግኘት LEA ምክንያታዊ የሆኑ ጥረቶች ሰነዶችን ማሰባሰብ አለበት። ሰነድ ማሰባሰቡ በጉዳዩ ዙሪያ የLEA ያደረጋቸውን እንደሚከተሉት ያሉ ሙከራዎችን ሪከርድ ያካተተ መሆን ይገባዋል፡-

- የተደረጉ የስልክ ጥሪዎች እና ሙከራዎች ዝርዝር ሪኮርድ፣ እና የእነኛ ጥሪዎች ውጤቶች፤
- ለእርስዎ የተላኩ ደብዳቤዎች ቅጂዎች እና ማንኛውም የተቀበሉዋቸው ምላሾች፤ <u>እና</u>
- በእርስዎ ቤት የተደረጉ ጉብኝቶች ዝርዝር ሰነዶች ወይም የቅጥር ቦታ እንዲሁም የእነኛ ጉብኝቶች ውጤቶች።

***ሌሎች የስምምነት መስፈርቶች***

LEA የሚከተሉትን የሚያከናውን ከሆነ የእርስዎ ስምምነት አያስፈልግም ፡-

- አሁን ያለውን ዳታ እንደ ልጅዎ ግምገማ ወይም ዳግም ግምገማ አካል ይከልሱ፤ <u>ወይም</u>
- ከዚህ በፊት ሙከራ ወይም ግምገማ ካልወሰደ/ች በቀር ለሁሉም ልጆች የሚሰጠውን ሙከራ ወይም ግምገማ ለልጅዎ ይስጡ፣ ከሁሉም ልጆች ወላጆች ቅድመ ስምምነት ያስፈልጋል።

በራስዎ ወጪ ልጅዎን የግል ትምህርት ቤት አስመዝገበውት/ዋት ከነበረ ወይም ልጅዎን እቤት ውስጥ እያስተማሩት/ሯት ከሆነ እና ለልጅዎ የመጀመሪያ ግምገማ ወይም ዳግም ግምገማ ስምምነትዎን ካልሰጡ፣ ወይም ስምምነትዎን ለመስጠት የተጠየቁትን ጥያቄ ካልመለሱ፣ LEA የግጭት መፍቻ አካሄዶቹን ላይጠቀም ይችላል (ለምሳሌ እንደ ማደራደር፣ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ፣ የመፍትሄ ስብሰባ፣ ወይም ገለልተኛ የአቤቱታ መስሚያ ሂደት የመሰሳሰሉት)እና ልጅዎ እኩል አገልግሎቶችን (አገልግሎቶቹ ለጥቂት በወላጆች ለተመደቡ የግል ትምህርት ቤት ውስጥ ላሉ አካል ጉዳተኛ ልጆች እንዲኖር ተደርጓልፅ እንዲያገኝ/ድታገኝ ብቁ እንደሆነ/ች መቁጠር አይጠበቅበትም።

## ገለለተኛ የትምህርት ግምገማዎች

**34 CFR §300.502**

**ፍቺ**

*ገለልተኛ የትምህርት ግምገማዎች* (*independent educational evaluation* (IEE)) LEA በተቀጠረ ለልጅዎ ትምህርት ሃላፊነት በተሰጠው ብቃት ባለው ፈታኝ የሚከናወን ግምገማ ነው።ከዚህ በታች እንደተገለፀው፣ በ LEA በተከናወነው የግምገማ ውጤቶች ካልተስማሙ IEE የመቀበል መብት አለዎ። If you request an IEE ከጠየቁ፣ የተሳተፈው LEA IEE የት ሊያገኙ እንደሚችሉ እና ለIEEዎች ለማመልከት ስለ LEA መስፈርቶች መረጃ ሊሰጥዎ ይገባል።

*የህዝብ ወጭዎች* ማለት አንድም LEA የግምገማውን ሙሉ ወጭ በሚከፍል ጊዜ አልያም ግምገማው ካለምንም ወጭ መከናወኑን በሚያረጋግጥ ጊዜ ነው። ይህ አቅርቦት የIDEA ክፍል B ያካተተ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ግዛት የክፍል B መስፈርቶች ለማሟላት የግዛት፣ አካባቢያዊ፣ ፌደራል እና ያሉትን የግል የድጋፍ ምንጮችን መጠቀም እንደሚችሉ ይፈቅዳል።

***በህዝብ ወጪ የወላጆች ግምገማ መብት***

የሚከተሉት ሁኔታዎች የሚፈፀሙ ከሆነ ከLEA በተገኘው የግምገማ ውጤት ካልተስማሙ በህዝብ ወጭ ልጅዎን IEE የማድረግ መብት አለዎ፡

***በህዝብ ወጭ ለልጅዎ ገለልተኛ የትምህርት ግምገማ ጠይቀው ከሆነ፣ የእርስዎ LEA ካለአስፈላጊ መዘግየት <u>አንድም፤</u> (ሀ) የልጅዎ ግምገማ አግባብ ያለው እንደሆነ መላሳየት ይግባኝ ለመጠየቅ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ማስገባት አለበት፤ አልያም (ለ)ችሎት ላይ እርስዎ ያቀረቡት የልጅዎ ግምገማ የ LEA መስፈርት የማያሟላ እንደሆነ ካላሳየ በስተቀር LEA በህዝብ ወጭ ገለልተኛ የሆነ የትምህርት ግምገማ ማቅረብ አለበት።***

- የእርስዎ LEA ይግባኝ ከጠየቀ እና የመጨረሻው ውሳኔ LEA ለልጅዎ ያደረገው ግምገማ አግባብ ያለው እንደሆነ ከተወሰነ፣ አሁንም IEE የማግኘት መብት አለዎ፣ ሆኖም ግን በህዝብ ወጭ የሚሸፈን አይደለም።

- ለልጅዎ IEE ከጠየቁ፣ በLEA የተገኘውን የልጅዎን ግምገማ ለምን እንደተቃወሙ LEA ሊጠይቅዎ ይችላል። ሆኖም ግን፣ LEA ማብራሪያ ላይፈልግ ይችላል እና ያለ አግባብ ለልጅዎ IEE በህዝብ ወጭ እንዳይሰጥ ላያዘገይ ይችላል ወይም በልጅዎ ላይ LEA ያደረገውን ግምገማ ውጤት ለመከላከል ይግባኝ ለመጠየቅ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታን አያስገባም።

በየጊዜው LEA በልጅዎ ላይ ግምገማ በሚያከናውን ጊዜ እና እርስዎ ባልተስማሙት ላይ በህዝብ የሚሸፈን ወጭ ለልጅዎ የሚፈቀደው አንድ ብቻ IEE ነው።

**በወላጅ አነሳሽነት የሚከናወኑ ግምገማዎች**

በህዝብ በተሸፈነ ወጭ የልጅዎን IEE ካገኙ ወይም በግል ወጭዎ ያከናወኑትን የልጅዎን ግምገማ ከLEA ጋር ከተጋሩ፣ የሚከተሉት በስራ ላይ ይውላሉ:-

- የልጅዎ ግምገማ ውጤት ፣ ከFAPE የልጅዎ አቅርቦት ጋር በሚደረግ በማንኛውም ውሳኔ ውስጥ LEA ለIEEዎች ያስቀመጣቸውን መስፍርቶች የሚያሟላ ከሆነ LEA ከግምት ማስገባት አለበት፤ <u>እና</u>
- እርስዎ ወይም የLEA ልጅዎን በተመለከተ ግምገማውን በይግባኝ ሂደት ውስጥ እንደ ምስክርነት ማቅረብ ትችላላችሁ።

**በይግባኝ ሰሚ መኮንኖች የሚጠየቅ የግምገማዎች ጥያቄ**

ይግባኝ ሰሚ መኮንን እንደ ይግባኝ መስሚያ ሂደቱ የልጅዎን IEE ከጠየቀ/ች፣ የግምገማው ክፍያ በህዝብ ወጭ የሚሸፈን ይሆናል።

**LEA መስፈርት**

IEE በህዝብ ወጭ የሚሸፈን ከሆነ፣ ግምገማው ተቀባይነት የሚያገኝበት መስፈርት፣ የግምገማውን ቦታ እንዲሁም የፈታኙን ብቃት ጨምሮ፣ LEA ግምገማን በሚጠይቅ ጊዜ ከሚጠቀማቸው መስፈርቶች ጋር ተመሳሳይ መሆን ይገባቸዋል(መስፈርቶቹ እርስዎ IEE ከማግኘትዎ መብት ጋር ተመሳሳይ እስከሚሆን ድረስ ሊሄድ ይችላል)።

ከላይ ከተዘረዘረው መስፈርት በስተቀር፣ LEA ሁኔታዎች ላይ ጫና አያደርግም ወይም በህዝብ ወጭ በሚገኝ IEE የጊዜ ሰሌዳ እና ተዛማጅ ነገሮች ላይ ጫናን አይፈጥርም።

## *የመረጃ ሚስጥራዊነት*

### ፍቺዎች

### 34 CFR §§300.611 and 300.32

**በመረጃ ሚስጥራዊነት** ርዕስ ስር በአገልግሎት እንደዋለው:-

- *ጥፋት ማለት* አካላዊ ጥፋት ወይም የግለሰብ ማንነትን ከመረጃ ላይ ማስወገድ ነው ስለዚህም መረጃው ከዚህ በኋላ በግለሰብ ደረጃ የማይታወቅ ይሆናል።

- *የትምህርት ሰነዶች* ማለት በ34 CFR ክፍል 99 ውስጥ «ትምህርት ሰነዶች» ስር የሚሸፈን የትምህርት ሰነዶች አይነት ነው (የ1974ቱ ቤተሰብ ትምህርት መብቶችን እና ግላዊነት አዋጅ፣ 20 U.S.C. 1232g (FERPA))።

- *ተሳታፊ ኤጀንሲ* ማነት ማንኛውም የትምህርት ቤት አውራጃ፣ ኤጀንሲ ወይም በግል የሚለይ መረጃን የሚሰበስብ፣ም የሚያስቀምጥ ወይም የሚጠቀም ተቋም ማለት ነው፣ አልያም ደግሞ በIDEA ክፍል B መረጃ የሚሰበሰብበት አካል ነው።

- *በግል የሚለይ መረጃ* ማለት የሚከተሉን መረጃዎች የሚያካትት ነው:-

(ሀ) የልጅዎ ስም፣ የእርስዎ ስም እንደ ወላጅ፣ ወይም የሌላ የቤተሰብ አባል ስም፤

(ለ) የልጅዎ አድራሻ፤

(ሐ) እንደ የልጅዎ ማህበራዊ ደህንነት ቁጥር ወይም የተማሪ መለያ ቁጥር የመሳሰሉ የግል መለያዎች፤ ወይም

(መ) የግል ባህሪያት ዝርዝር ወይም ልጅዎን አመንክዮአዊ በሆነ እርግጠኝነት ለመለየት የሚያስችሉ ሌሎች መረጃዎች።

## ለወላጆች ማሳወቂያ

### 34 CFR §300.612

ስለ ግለሰብ መለያ መረጃ ሚስጥራዊነት ሙሉ በሙሉ የሚያሳውቅዎ OSSE፣ እንደ SEA፣ በቂ የሆነ ማሳወቂያ ለእርስዎ ማስጠት ይገባዋል፡-

- በኮሎምቢያ አውራጃ ውስጥ ማሳወቂያው በበርካታ ህዝቦች የአፍ መፍቻ ቋንቋ እስከ ምን ድረስ እንደሚሰጥ የሚያሳውቅ ዝርዝር፤
- በግል የሚለዩ መረጃዎች የሚቀመጥባቸው ልጆች ዝርዝር፣ የሚጠየቀው መረጃ፣ መረጃውን ለመሰብሰብ የኮሎምቢያ አውራጃ ለመጠቀም ያቀደው ዘዴዎች (መረጃዎቹ የሚሰበሰብባቸውን ምንጮች ጨምሮ)፣ እና የመረጃው ጥቅም፤
- ተሳታፊ ኤጀንሲዎች ማከማቸትን፣ ለሶስተኛ ወገን ማሳወቅን፣ ማቆየትን፣ እና በግል የሚለይ መረጃ የማጥፋትን የተመለከቱ የፓሊሲዎች እና አካሄዶች ማጠቃለያ፤ እና
- በቤተሰብ የትምህርት መብት እና ግላዊነት አዋጅ (Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)) እና 34 CFR ክፍል 99 በስራ ላይ የሚውልበትን ደንቦች ጨምሮ ይህን መረጃ በተመለከተ የወላጆች እና የልጆች ሁሉም መብት ዝርዝር።

ልዩ የትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን (*ልጆች መፈለግ* (*Child Find*) ተብሎም ይታወቃል) የሚፈልጉ ልጆችን ከመለየት፣ ከማግኘት፣ ወይም ከመገምገማችን እና ከማንኛውም ዋና እንቅስቃሴ በፊት፣ ማሳወቂያው በጋዜጣዎች እና/ወይም በሌሎች መገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች መታተም ወይም መተዋወቅ አለበት፣ ስርጭቱም ወላጆችን በበቂ ሁኔታ እንዲያሳውቅ በኮሎምቢያ አውራጃ በአጠቃላይ ይህን እንቅስቃሴ በሚያደርጉ ሁሉ መከናወን አለበት።

## የማግኘት መብቶች

### 34 CFR §300.613 እና 5E DCMR §2600.2

ተሳታፊው ኤጀንሲ ማንኛውንም ከልጅዎ ጋር ተያያዥ የሆኑ እና የተሰበሰቡ፣ የተቀመጡ ወይም በእርስዎ LEA ክፍል B፣ IDEA በአገልግሎት ላይ የዋሉ የትምህርት ሰነዶችን እንዲመረምሩ እና እንዲከልሱ መፍቀድ ይገባዋል። ተሳታፊው ኤጀንሲ ካለ ምንም መዘግየት እና IEP በተመለከተ ከሚደረግ ማንኛውም ስብሰባ በፊት ማንኛውንም የልጅዎን የትምህርት ሰነዶች እንዲመረምሩ እና እንዲከልሱ ፣ ወይም ጥያቄዎን ባቀረቡ ከአርባ አምስት (45) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ማንኛውም ገለልተኛ በሂደት ላይ ያለ የአቤቱታ መስሚያ (የመፍትሄ መስጫ ስብሰባን ወይመ ስነምግባርን በተመለከተ የሚደረግ ችሎት) የጠየቁትን ጥያቄ ለማስተናገድ ይገባዋል።

የትምህርት ሰነዶችን የመመርመር እና የመከለስ መብት የሚከተለውን ያካትታል፡

- አመንክዮአዊ ማብራሪያ እና ፍቺዎችን ለጠየቁባቸው ሰነዶች ከተሳታፊ ኤጀንሲ መልስ የማግኘት መብትዎ፤
- የልጅዎን የትምህርት ሰነዶች የመመርመር እና የመከለስ መብትዎ በንኡስ ርዕስ ***ክፍያዎች*** ስር እንደተገለፀው ምክንያታዊ ክፍያን በመክፈል የመረጃዎችን ቅጂ የማግኘት መብትን ያካትታል፤ እና
- የእርስዎ ህጋዊ ተወካይ ሰነዶቹን የመመርመር እና የመከለስ መብትዎ።

ተሳታፊ ኤጀንሲው በስራ ላይ ባለው እንደ ማሳደግ፣ መለያየት፣ እና/ወይም ፍቺን በሚያየው የኮሎምቢያ አውራጃ ህግ ስር እርስዎ ስልጣን እንደሌልዎ ካልተገለፀለት በስተቀር ከልጅዎ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሰነዶችን የመመርመር እና የመከለስ ስልጣን እንዳለዎ ሊገምት ይችላል።

## ሰነዶች ማግኘት

### 34 CFR §300.614

እያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጀንሲ የትምህርት ሰነዶችን የሚያገኙ፣ የሚሰበስቡ፣ የሚያስቀምጡ፣ ወይም ወይም በIDEA ክፍል B ስር የሚጠቀሙ አካላትን መመዝገብ አለበት፣ (ይህም በወላጆች እና ፈቃድ ባላቸው የተሳታፊ ኤጀንሲ ተቀጣሪዎች ካልሆነ በቀር)፣ ሰነዶቹን ያገኘው አካል ስም፣ እንዲያገኙ የተሰጠበት ቀን፣ እና የሚመለከተው አካል ሰነዶቹን እንዲያገኝ የተፈቀደበትን ምክንያት የሚያካትት ይሆናል።

## ከአንድ ልጅ በላይ ያሉ ሰነዶች

**34 CFR §300.615**

ማንኛውም የትምህርት ሰነድ ከአንድ ልጅ በላይ መረጃን ከያዙ፣ ከልጅዎ ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን የመመርመር፣ የመከለስ፣ እና የማወቅ መብት አለዎ።

## የመረጃ ዝርዝር ዓይነቶች እና የሚገኙበት ስፍራዎች

**34 CFR §300.616**

በሚጠየቅ ጊዜ፣ እያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጀንሲ የተሰበሰቡ፣ የተቀመጡ ወይም በኤጀንሲው በአገልግሎት ላይ የዋሉ የመረጃዎዝን ዝርዝር ዓይነቶች እና የሚገኙበትን ስፍራዎች ሊሰጥዎ ይገባል፡፡

## ክፍያዎች

**34 CFR §300.617**

ክፍያው ሰነዶችን የመመርመር እና የመከለስ መብትዎን በሚገባ እንዳያከናውኑ የሚያግድዎት ከሆነ፣ እያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጀንሲ በIDEA ክፈል B ስር ለእርስዎ የተደረጉትን የሰነዶች ቅጂ አግባብ ያለው ክፍያን ሊያስከፍል ይችላል።

በIDEA ክፈል B ስር ተሳታፊው ኤጀንሲ መረጃን ለመፈለግ እና ለማውጣት ክፍያን ላያስከፍል ይችላል።

## በወላጆች ጥያቄ መሰረት ሰነዶችን ማሻሻል

**34 CFR §300.618**

ልጅዎን የሚመለከት በትምህርት ሰነዶች ውስጥ ያለ መረጃ የተሰበሰበ፣ የተቀመጠ፣ ወይም በIDEA ክፈል B ስር በአገልግሎት ላይ የዋለ መረጃ ትክክል ያልሆነ፣ አሳሳች፣ ወይም የልጅዎን ግላዊነት እና ሌሎች መብቶች የሚጥስ ነው ብለው ካመኑ፣ መረጃውን ያስቀመጠውን ተሳታፊ ኤጀንሲ መረጃውን እንዲቀይር መጠየቅ ይችላሉ።

ተሳታፊው ኤጀንሲ ጥያቄዎን በተቀበለ አግባብ ባለው ጊዜ ውስጥ በጥያቄዎ መሰረት መረጃውን ለመቀየር መወሰን ወይም አለመወሰን ይገባዋል።

ተሳታፊው ኤጀንሲ መረጃውን በጥያቄዎ መሰረት ለመቀየር ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ፈቃደኛ አለመሆኑን ለእርስዎ ማሳወቅ ይገባዋል እንዲሁም ***በችሎት እድል*** ርዕስ ስር በተገለፀው መሰረት ይግባኝ የማለት መብት እንደሚችሉ ይመክርዎታል።

## የችሎት እድል

**34 CFR §300.619**

ተሳታፊው ኤጀንሲ፣ ሲጠየቅ፣ በትምህርት መዝገቦች ውስጥ የተቀመጡት ልጅዎን የሚመለከቱ መረጃዎች ትክክል ያልሆኑ፣ የሚያሳስቱ፣ ወይም የልጅዎን የግላዊነት ወይም ሌሎች መብቶች የሚተላለፉ እንዳይሆኑ መረጃዎቹን የሚፈትኑበት የችሎት እድል ማቅረብ አለበት፡፡

## የችሎት አኪያሄዶች

**34 CFR §300.621**

የትምህርት መዝገቦች ውስጥ ያሉ መረጃዎች ላይ ጥያቄ የማቅረቢያ ችሎት በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት አዋጅ (Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)) ስር ለእንደዚህ አይነት ችሎት አኪያሄድ በተቀመጠው መሰረት መኪያሄድ አለባቸው፡፡

## የችሎት ውጤት

**34 CFR §300.620**

በችሎቱ ውጤት መሰረት፣ ተካፋዩ ኤጀንሲ መረጃው ትክክል ያልሆነ፣ አሳሳች ወይም የግላዊነት ፖሊሲን ወይም የልጅዎን ሌሎች መብቶች የሚተላለፍ ነው ብሎ ከወሰነ በተመሳሳይ መረጃውን መለውጥ እና እርስዎን በጽሁፍ ማሳውቅ አለበት፡፡

በችሎቱ ውጤት መሰረት፣ ተካፋዩ ኤጀንሲ መረጃው ትክክል ነው፣ አሳሳች ወይም የግላዊነት ፖሊሲን ወይም የልጅዎን ሌሎች መብቶች የሚተላለፍ አይደለም ብሎ ከወሰነ በልጀዎ ላይ ኤጀንሲው በያዘው መረጃ ላይ አስተያየት የመስጠት ወይም በተሳታፊ ኤጀንሲው ውሳኔ ላይ ያልተሳማሙበትን ምክንያት የማቅረብ መብቶችዎን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

እንዲዚህ አይነት ማብርሪያ :

- እንደ ልጅዎ ምዝገባ አካል በተሳታፊው ኤጀንሲ የተያዘ እና ምዝገባው ወይም ጥያቄ የቀረበበት ክፍል በተሳታፊው ኤጀንሲ የተያዘ መሆን አለበት፣ እና
- ተሳታፊው ኤጅነሲ የልጅዎን ምዝገባዎች ወይም ጥያቄ የቀረባበቸውን መረጀዎች ለማንኛውም ወገን ከገለጸ፣ ማብራሪያውም አብሮ መቅረብ አለበት፡፡

## የግል ማንነትን ሊገልጹ የሚችሉ መረጀዎችን የመግለጽ ስምምነት

**34 CFR §300.622**

መረጃው በትምህርት መዛግብት ውስጥ የተያዘ ካልሆነ እና በቤተሰብ ትምህርት መብቶች ግላዊነት አዋጅ (Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)) መስረት ያለቤተሰብ ስምምነት ለመግለጽ ስልጣን ካልተሰጠ በስተቀር፣ በግል ማንነትን ሊገልጹ የሚቸሉ መረጃዎች ከተሳታፊው ኤጀንሲ መኮንኖች ውጪ ለሌላ አካል አሳልፎ ከመስጠት በፊት የእርስዎ ስምምነት መገኘት አለበት፡፡ ከዚህ በታች ከተለዩት ሁኔታዎች ውጪ፣ በግል ማንነትን ሊገልጹ የሚችሉ መረጀዎች የ IDEA ክፍል B መሰፈርቶች መሰረት ለስብሰባ ጉዳይ ለተሳታፊ ኤጀንሲዎች ባለስልጣናት ከመገለጻቸው በፊት የእርስዎ የቅድሚያ ስምምነት አይጠየቅም፡፡

የግል ማንነትን ሊገልጹ የሚችሉ መረጃዎች የሽግግር አገልግሎቶች ለሚያቀርቡ ወይም ለሽግግር አገልግሎቶች ለሚከፍሉ ታሳታፊ ኤጀንሲዎች ከመገለጹ በፊት የእርስዎ ስምምነት፣ ወይም በኮሎምቢያ አውራጃ ህግ መሰረት ለአዋቂነት የእድሜ ደረጃ (አስራ ስምነት (18) አመት) የደረሰ ብቁ ልጅ ስምምነት መገኘት አለበት፡፡

ልጁ እርስዎ በሚኖሩበት LEA ውስጥ ያልሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር ከሆነ ወይም ሊማር ከሆነ የግል ትምህርት ቤቱ ባለበት LEA እና እርሶ በሚኖሩበት LEA ባለስልጣናት መካከል ማንኛውም በግል ማንነትን ሊገልጹ ሚችሉ መረጃዎች ልውውጥ ከመደረጉ በፊት የእርስዎ ስምምነት መገኘት አለበት፡፡

## ጥብቃዎች

**34 CFR §300.623**

እያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጅንሲ በግል ማንነትን ሊገልጹ የሚችሉ መረጃዎችን በሚሰበስብበት፣ በሚያመከማችበት፣ በሚገልጽበት እና በሚስወግድበት ጊዜ ሚስጥራዊነታቸወን መጠበቅ አለበት፡፡ በግል ማንነትን ሊገልጹ የሚችሉ መረጃዎችን ሚስጥራዊነት ለማረጋገጥ በእያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጅንሲ ወስጥ አንድ ባለስልጣን ሃላፊነት መውሰድ አለበት፡፡ በግል ማንነትን ሊገልጹ የሚችሉ መረጀዎች ላይ የሚሰሩ ሁሉም ግለሰቦች የ IDEA እና FERPA ክፍል B ስር ሰለኮሎምቢያ አውራጃ ፖሊሲዎች እና አኪያሄዶች ልምምድ ወይም መመሪያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ እያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጅንሲ፣ ለህዝብ ምርመራ፣ በግል ማንነትን ሊገልጹ የሚችሉ መረጃዎች ላይ ሊደርስ የሚችሉ አሁን ያሉትን የኤጀንሲ ተቀጣሪዎች ሰምና የሰልጣን ደረጃ የሚገልጽ ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡

## መረጀዎች ማስወገድ

**34 CFR §300.624**

በግል ማንነትን ሊገልጹ የሚችሉ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማያዝ፣ ወይም በIDEA ክፍል B መሰረት ለልጅዎ የትምህርት አገልግሎቶች ለማቅረብ አስፈለጊ በማይሆንበት ጊዜ LEA ለእርሰዎ ማሳወቅ አለበት፡፡

መረጃው በእርሶ ጥያቄ መደምሰስ አለበት፡፡ ሆኖም ግን የልጅዎ ቋሚ ምዝገባ ስም፣ አድራሻ እና ስልክ ቁጥር፣ ክፍሎች፣ የተሳተፈባቸው መዘገብ፣ የተማረባቸው ክፍሎች፣ ያጠናቀቀው የትምህርት ደረጃ፣ እና ያጠናቀቀበት አመት ያለጊዜ ገደብ ይቀመጣሉ፡፡

# የአቤቱታ አካሄዶች

## በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ መስሚያ እና በግዛት አቤቱታ አካሄዶች መካከል ያለ ልዩነት

የIDEA ክፍል B ለግዛት አቤቱታ እና በሂደት ላይ ላለ የአቤቱታ መስሚያዎች የተለያዩ አካሄዶችን አስቀምጧል። ከዚህ በታች እንደተብራራው፣ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የIDEA ክፍል B እና/ወይም በLEA፣ OSSE፣ ወይም በማንኛውም የህዝብ ኤጀንሲ የሚሰጥ ልዩ ትምህርትን በተመለከተ የኮሎምቢያ አውራጃን ህግ ማንኛውም መስፈርት እንደተጣሰ በመግለፅ የግዛት አቤቱታ ማስገባት ይችላሉ። የመለያ ለውጥ ጥያቄ ወይም ፈቃደኛ አለመሆን፣ ግምገማ፣ ወይም የአካል ጉዳተኛ ልጅን የትምህርት ምደባን፣ ወይም ለአንድ ልጅ የነፃ እና አግባብ ያለው የህዝብ ትምህርት አሰጣጥን እና የመሳሰሉትን ተዛማጅ ጉዳዮች በተመለከተ እርስዎ ወይም LEA ብቻ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታን ማቅረብ ትችላላችሁ። ይህም ሲሆን የOSSE ሰራተኛ የጊዜ ገደቡ በሚገባ ካልተራዘመ በቀር፣ ገለልተኛ የሆነ የአቤቱታ ሰሚ መኮንን አቤቱታውን መስማት የሚገባው ካልሆነ በቀር (በመፍትሄ መስጫ ስብሰባ ጊዜ መፍትሄ ካላገኘ ወይም በድርድር ካልተፈታ) በአጠቃላይ በስልሳ (60) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የግዛት አቤቱታውን መፍታት ይገባዋል እንዲሁም መፍትሄ የመስጫው ጊዜ ካበቃ በኋላ በዚህ ሰነድ የመፍትሄ አሰሰጣጥ ሂደት በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለፀው፣ አቤቱታ ሰሚው መኮንን በእርስዎ ወይም በLEA ጥያቄ መሰረት ለተወሰነ የጊዜ ገደብ ማራዘሚያን ካልሰጠ በቀር በአርባ አምስት (45) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ በፅሁፍ የቀረበ ውሳኔ መስጠት አለበት። የግዛት አቤቱታ እና በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ፣ መፍትሄ አሰጣጥ እና ችሎት በበለጠ ከዚህ በታች ተብራርቷል። የOSSE በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ለማስገባት የሚያግዝዎ ሞዴል ቅፅ ማዘጋጀት ይገባዋል እንዲሁም እርስዎንም ሆነ ሌላኛዎቹን ወገኖች ***በሞዴል ቅጾች*** ርዕስ ስር በተገለፀው መሰረት የግዛት አቤቱታ እንድታስገቡ ሊያግዛችሁ ይገባል።

## የግዛት አቤቱታ አካሄዶች አቀባበል

### 34 CFR §300.151

OSSE ለሚከተሉት በፅሁፍ የቀረቡ አካሄዶች ሊኖረው ይገባል፦

- በድርጅት ወይም በሌላ ግዛት ውስጥ ካለ ግለሰብ የሚገባን ማንኛውንም አቤቱታ መፍታት፤
- አቤቱታ ለOSSE ማስገባት፤ <u>እና</u>
- የግዛት አቤቱታ አካሄዶችን ለወላጆች እና ለሌሎች ፍላጎት ላላቸው ግለሰቦች፣ ለቤተሰብ ስልጠና እና የመረጃ ማዕከላት፣ የጥበቃ እና ውትወታ ኤጀንሲዎች፣ ገለልተኛ የመኖሪያ ማዕከላት፣ እና ለሌሎች አግባብ ያላቸው አካላት በስፋት የማሰራጨት።

#### አግባብ ያላቸው አገልግሎት በሚከለከል ጊዜ የሚወሰዱ መፍትሄዎች

OSSE ተገቢውን አገልግሎቶች ለማቅረብ ሳይሳካ ያገኘውን የግዛት አቤቱታን በመፍታት ውስጥ፣ አግባብ ያለው አገልግሎት ለመስጠት OSSE ላልተሳካው ነገር መፍትሄን መስጠት ይገባዋል፤ ይህም የአንድ ልጅን ፍላጎት ለማሟላት አግባብ ያለው እርምት የተወሰደበት እርምጃ መውሰድን ያጠቃልላል (እንደ የማካካሻ አገልግሎቶች ወይም የገንዘብ ካሳ)፣ እና ለሁሉም አካል ጉዳተኛ ልጆች ለወደፊት የሚሰጡ አግባብ ያላቸው አገልግሎቶችን ማቅረብ፡፡

## የግዛት ዝቅተኛ አቤቱታ አካሄዶች

### 34 CFR §300.152 እና OSSE መደበኛ የግዛት አቤቱታ ፓሊሲ እና አካሄዶች

#### የጊዜ ገደባ፤ ዝቅተኛ አካሄዶች

አቤቱታ ከገባ በኋላ OSSE በግዛት አቤቱታ አካሄዶች ውስጥ ስልሳ (60) የቀን መቁጠሪያ ቀናትን ማካተት ይገባዋል፣ የሚከተሉትንም ከግምት ያስገባል፦

- ገለልተኛ የሆነ በቦታው ላይ ምርመራን ለማከናወን፣ OSSE ምርመራ አስፈላጊ ነው ብሎ ከወሰነ፤
- አቤቱታ አቅራቢው አካል በአቤቱታው ውስጥ ስላለው ክስ፣ በቃል ወይም በጽሁፍ ተጨማሪ መረጃዎችን እንዲያስገባ እድል መስጠት፤
- LEA ወይም ሌላ የህዝብ ኤጀንሲ ለአቤቱታው ምላሽ እንዲሰጡ እድል ይስጧቸው፣ ቢያንስ የሚከተለውን ጨምሮ፦ (ሀ) በኤጀንሲው አማራጭ፣ አቤቱታውን ለመፍታት የሚያስችል ሃሳብ፤ <u>እና</u> (ለ) አቤቱታ ላስገበው ወላጅ እና ኤጀንሲው ለድርድር በፍላጎት እንዲገቡ እድል መስጠት፤
- ሁሉንም ተዛማጅ መረጃ መከለስ እና LEA ወይም የህዝብ ኤጀንሲ የ IDEA ክፍል B ወይም የኮሎምቢያ አውራጃን ልዩ የትምህርት ህግ መስፈርትን ጥሰው እንደሆነ ገለልተኛ ውሳኔን ይወስኑ፤ <u>እና</u>

- በአቤቱታው ውስጥ ለእያንዳንዱ ክስ ምላሽ የሚሆን ውሳኔን በፅሁፍ ይስቱ እና የሚከተሉትን ያካቱ (ሀ) የተገኙ እውነቶችን እና ድምዳሜዎችን እና (ለ) የOSSEን የመጨረሻ ውሳኔ ምክንያቶች።

ውሳኔው ለአቤቱታ አቅራቢው እና ተሳታፊ ለሆነው የህዝብ ኤጀንሲ ይላካል።

### የጊዜ ማራዘም፤ የመጨረሻ ውሳኔ፤ በተግባር ላይ ማዋል

ከላይ የተገለፁት የOSSE አካሄዶች የሚከተሉንም ከግምት ማስገባት አለባቸው፡-

- በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ለስልሳ (60) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ማራዘምን መፍቀድ፡-

    a. በተወሰነ የግዛት አቤቱታ ልዩ የሆኑ ሁኔታች ይኖራሉ፤ ወይም
    b. እርስዎ እና LEA ወይም ሌላ ተሳታፊ የህዝብ ኤጀንሲ በድርድር ወይም በግዛት ውስጥ ካሉ በአማራጭ ግጭት መፍቻ መንገዶች ጉዳዩን ለመፍታት የተያዘውን ጊዜ በፈቃደኝነት ለማራዘም ተስማምተዋል።

- የ OSSEን የመጨረሻ ውሳኔ በሚገባ በስራ ላይ ለማዋል አካሄዶችን ማካተት፣ አስፈላጊ ከሆነ የሚከተሉን ጨምሮ፡-
    a. የቴክኒክ እገዛ እንቅስቃሴዎች፤

    b. ድርድሮች፤ እና

    c. ስምምነት ላይ ለመድረስ የእርምት እርምጃዎች።

### የግዛት አቤቱታዎች እና በሂደት ላይ ያሉ ችሎቶች

በጽሁፍ የቀረበ አቤቱታ ከተቀበሉ ***በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ማስገባት*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው እርሱም የችሎቱ አካል ነው፣ ወይም የግዛት አቤቱታው የእነኝህን ችሎቶች አንድ ወይም ተጨማሪ ክፍሎች በርካታ ጉዳዮችን ስለሚያካትት፣ OSSE መፍትሄ የተሰጠውን ማንኛውንም አይነት የግዛት አቤቱታ ችሎቱ እስኪያበቃ ድረስ ወደ ጎን ማድረግ ይገባዋል። ማንኛውም በግዛት አቤቱታ ውስጥ ያለ ጉዳይ እና በሂደት ላይ ያለ አ

በግዛት አቤቱታ የተነሳው ጉዳይ ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ አካላትን አካቶ በሂደት ላይ ባለ ችሎት ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ (ለምሳሌ እርስዎ እና LEA)፣ በዚያ ጉዳይ ላይ በሂደት ላይ ባለ የተሰጠው ውሳኔ የሚጸና ይሆናል እና OSSE ለአቤቱታ አቅራቢው ውሳኔው እንደሚጸና ማሳወቅ ይገባዋል።

A complaint alleging an በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ መስሚያ ችሎት መፍትሄ የሚሰጠውን የማስፈፀሚያ ስምምነት LEA ወይም የህዝብ አጄንሲ በአግባቡ በስራ ላይ እንዳላዋሉ የሚያትት አቤቱታ ከቀረበ በግዛት አቤቱታ ሂደት ሊፈታ ይችላል ሆኖም ግን የግዛት አቤቱታ ሂደቱ መኖር እና የማስፈፀሚያ ስምምነቱን በስራ ላይ እንዳልዋለ በሚቀርብ ክስ አቤቱታ አቅራቢው ወገን ተመሳሳይ የህግ ስልጣን ካለው ፍርድ ቤት ስምምነቱ እንዲፈፀም የማስገደድ መብቱ  የተጠበቀ ነው ወይም አይከለከልም።

### የግዛት አቤቱታ ማስገባት

---

### 34 CFR §300.153 እና መደበኛ የOSSE የግዛት አቤቱታ ፓሊሲ እና አካሄዶች

ድርጅት ወይም ግለሰብ ተፈርሞ በጽሁፍ የቀረበ አቤቱታ ከላይ በተገለፀው አካሄዶች መሰረት ማስገባት ይችላሉ።

የግዛት አቤቱታ የሚከተሉትን ማካተት ይገባዋል፡-

- A statement that the LEA ወይም ሌላ የህዝብ ኤጀንሲ የIDEA ክፍል Bን መስፈርት ወይም በ34 CFR ክፍል 300 ውስጥ በተግባር ላይ የሚውልበትን  እና/ወይም ልዩ ትምህርትን በተመለከተ የኮሎምቢያ አውራጃ ህግ ጥሰትን የሚያቀርብ መግለጫ፤
- መግለጫው መሰረት ያደረገባቸው እውነታዎች፤

- አቤቱታውን የሚያስገባው አካል ፊርማ እና የሚገኙበት አድራሻ፤ እና

- ተፈጽሟል የተባለው ክስ አንድ ልጅን የተመለከተ ከሆነ፣ አቤቱታም መካተት ይገባዋል፡-

    ሀ. የልጁ/ቷ ስም እና የመኖሪያ አድራሻው/ዋ፤

    ለ. ልጁ/ቷ የሚማርበት/የምትማርበት ትምህርት ቤት፤

ሐ. ቤት ለሌለው ልጅ ወይም ወጣት (McKinney-Vento ቤት አልባዎች አዋጅ) የልጁን/ቷን አድራሻ እና ልጁ/ቷ የሚማርበት/የምትማርበት ትምህርት ቤት፤
መ. የልጁ/ቷ ችግር በዝርዝር፣ ከችግሩ ጋር ተያያዝነት ያላቸውን እውነታዎች ጨምሮ፤ እና
ሠ. ለችግሩ መፍትሄ የሚሆን ሃሳብ ይህም አቤቱታው በገባ ጊዜ አቤቱታውን የሚያስገባው አካል እስከሚያውቀው ገደብ ድረስ።

***የግዛት አቤቱታን አካሄዶችን በስራ ላይ ማዋል*** ርዕስ ስር እንደተገለጸው አቤቱታው ተቀባይነት ካገኘ ከአንድ አመት በላይ ያልሆነውን ጥሰት ማረጋገጥ ይገባዋል።

የግዛት አቤቱታውን ያስገባው አካል የአቤቱታውን ቅጂ ለLEA ወይም ልጁን/ቷን ለሚያስተናግድ ለሌላ የህዝብ ኤጀንሲ ማስተላለፍ አለበት በተመሳሳይም ለOSSE አቤቱታውን ያስገባል። አቤቱታው ከወላጅ ወይም ለአካለ መጠን ከደረሰ/ች ልጅ ያልገባ ከሆነ OSSE የአቤቱታውን ቅጂ ለወላጅ ወይም ለአካለ መጠን ለደረሰ/ች ልጅ ይልካል።

## በሂደት ላይ ያሉ አቤቱታ አኪያሄዶች

### በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ማስገባት

**34 CFR §300.507**

እርስዎ ወይም LEA በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ውስጥ ፣ የልጅዎን መለያ፣ ግምገማ ወይም የትምህርት ምደባን ወይም ለልጅዎ የሚቀርበውን FAPE ለመጠየቅ ወይም ፈቃደኛ ላለመሆን አቤቱታ ማስገባት ይችላሉ።

ያስታውሱ፣ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታን እድል ከማግኘትዎ በፊት እርስዎ እና ትምህርት ቤቱ/ LEA የመፍትሄ አሰጣጥ ስብሰባውን ካላነሳችሁት ወይም ወደ ድርድር ለመሄድ ካልወሰናችሁ በቀር፣ በመፍትሄ አሰጣጥ ስብሰባ ላይ ከትምህርት ቤቱ/ LEA ጋር በመገናኘት አቤቱታ የገባበትን ጉዳይ ለመፍታት መሞከር ያስፈልግዎታል።

በሂደት ላይ ያለው አቤቱታው ከሁለት (2) ዓመት ያልተከሰተ ጥሰትን ነው ማመላከት የሚገባው ይህም እርስዎ ወይም LEA በሂደት ላይ ስላለው አቤቱታ መሰረት ስለሆነው የተፈጸመ ድርጊት ታውቁ ነበር ወይም ማወቅ ይኖርባችሁ ነበር

በሚከተሉት ምክንያቶች በጊዜ ሰሌዳው መሰረት በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ማስገባት ከልቻሉ ከላይ ያለው የጊዜ ሰሌዳ በተግባር ላይ አይውልም:-

- በአቤቱታ ውስጥ የተጠቀሰውን ጉዳይ በተለይም LEA ጉዳዩን እንደፈታው አሳስቶ ካቀረበ፤ ወይም
- LEA በIDEA ክፍል B ውስጥ ለእርስዎ መስጠት ያስፈልግ የነበረውን መረጃ ካዘገየ።

***መረጃ ለወላጆች***

እርስዎ መረጃው ካስፈለግዎ LEA በአካባቢው የሚገኘውን ማንኛውንም ነፃ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ያለውን የህግ እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ሊያሳውቅዎ ይገባል፣ ወይም እርስዎ ወይም LEA በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ካስገባችሁ።

### በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ

**34 CFR §300.508**

ለአቤቱታ ቀጠሮ ለመጠየቅ፣ እርስዎ ወይም LEA (ወይም የእርስዎ ጠበቃ አልያም የLEA ጠበቃ) ለሌላኛው ወገን በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ማስገባት አለብዎ። አቤቱታው ሁሉንም (ከዚህ በታች የተዘረዘሩን) ይዘቶች ማካተት አለበት እና በሚስጥር ሊያዝ ይገባዋል። አስገቢው አካል የአቤቱታውን ቅጂ ለOSSE ማስገባት አለበት።

**የአቤቱታው ይዘት**

በሂደት ላይ ያለው አቤቱታ የሚከተሉን ማካተት ይገባዋል:-

- የልጁ/ቷ ስም፤
- የልጁ/ቷ መኖሪያ አድራሻ፤
- የልጁ/ቷ ትምህርት ቤት ስም፤
- የልጁ/ቷ መኖሪያ ቤት የሌለው/ላት ከሆነ/ች ወይም ወጣት ከሆነ/ች፣ የልጁ/ቷ አድራሻ መረጃ እና የትምህርት ቤቱ/ቷ ስም፤
- ከተጠየቀው ወይም ከተከለከለው ርምጃ ጋር በተያያዘ የልጁ/ቷ ችግር ሁኔታ ዝርዝር፣ ችግሩን በተመለከተ እውነታዎችን ጨምሮ፤ እና

- ለእግሩ እንደ መፍትሄ ይሆናል ተብሎ የቀረበ ሃሳብ ይህም በወቅቱ አቤቱታውን ያስገባው አካል (እርስዎ ወይም LEA) የማያውቀው እና ያላገኘው።

**በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ከመሰማቱ በፊት አስፈላጊ የሆነ ማሳወቂያ**

እርስዎ ወይም LEA (ወይም የእርስዎ ጠበቃ አልያም የLEA ጠበቃ) ከላይ የተዘረዘሩትን መረጃዎች ያካተት በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ካላስገባችሁ በቀር በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ መስሚያ ችሎት ላታገኙ ትችላላችሁ።

***የአቤቱታው የተሟላ/በቂ መሆን***

በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ወደ ፊት እንዲቀጥል፣ የተሟላ ሆኖ መገኘት ይገባዋል። በሂደት ላይ ያለው አቤቱታ የተሟላ ሆኖ የሚገኘው (ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ካሟላ ነው) በሂደት ላይ ያለውን አቤቱታ የሚቀበለው አካል (እርስዎ ወይም LEA) የአቤቱታ ሰሚ መኮንኑን <u>እና</u> ሌላኛውን ወገን አቤቱታውን እንደተቀበላችሁ በአስራ አምስት (15) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ በፅሁፍ ካላሳወቃችሁ በስተቀር፣ አቤቱታውን የሚቀበለው አካል በሂደት ላይ ያለው አቤቱታ ከላይ የተገለፁትን መስፈርቶች እንደማያሟላ ሊያምን ይችላል።

ማሳወቂያውን በተቀበላችሁ በአምስት (5) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የተቀበለው አካል በሂደት ላይ ያለውን አቤቱታ በቃ እንዳልሆነ ሊያገኘው ይችላል፣ አቤቱታ ሰሚው መኮንን በሂደት ላይ ያለው አቤቱታ ከላይ የተገለፁትን መስፈርቶች እንደሚያሟሉ መወሰን አለበት፣ እና ለእርስዎ እና ለLEA በፍጥነት በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።

***አቤቱታን ማሻሻል***

እርስዎ ወይም LEA በሚከተሉት ሁኔታዎች ለውጦችን ማከናወን ይችላሉ፦

- ሌላኛው ወገን ለውጡን በፅሁፍ ካጸደቀ እና በሂደት ላይ ያለ አቤቱታውን ከዚህ በታች ***በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት*** ንኡስ ርዕስ ስር እንደተገለጸው በውሳኔ መስጫ ስብሰባ እንዲፈታ ስልጣን ከተሰጠው፤ <u>ወይም</u>
- በሂደት ላይ ያለው አቤቱታ ከመጀመሩ ከአምስት (5) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ባልበለጠ የአቤቱታ ሰሚ መኮንኑ ለለውጦቹ ፈቃድ ከሰጠ።

በሂደት ላይ ባለው አቤቱታ ላይ አቤቱታውን ያስገባው አካል (እርስዎ ወይም LEA) ለውጥ ካደረጋችሁ፣ የተሻሻለው አቤቱታ በገባበት ቀን መሰረት የውሳኔ አሰጣጥ ስብሰባ የጊዜ ሰሌዳዎች (አቤቱታውን በተቀበሉ በአስራ አምስት (15)) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ) እና ለውሳኔ አሰጣጥ የጊዜ ገደቡ (አቤቱታውን በተቀበሉ በሰላሳ (30) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ) የተሻሻለው አቤቱታ ከገባበት ቀን በድጋሚ ይጀምሩ።

**በሂደት ላይ ላለ አቤቱታ የLEA ምላሽ**

በሂደት ላይ ባለው አቤቱታ ውስጥ የተካተተውን ርዕስ በተመለከተ ***በፅሁፍ የቀረበ ቅድመ ማስጠንቀቂያ*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለፀው LEA በፅሁፍ የቀረበ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ካላከልዎ፣ LEA በአስር (10) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የሚከተለውን ያካተተ ምላሽ ይልክልዎታል፦

- በሂደት ላይ ባለ አቤቱታ ውስጥ ርምጃ ለመውሰድ LEA ለምን ጥያቄ እንዳነሳ ወይም እንደከለከለ የሚገልፅ፤
- የIEP ቡድን ከግምት ውስጥ የሚያስገባው የሌሎች አማራጮች እና እነኛ ምክንያቶች ለምን እንደታገዱ የሚገልፅ ዝርዝር፤
- የእያንዳንዱ ግምገማ አካሄድ፣ አሰሳ፣ ሰነድ፣ ወይም LEA ለተጠየቀው ወይም ለተከለከለው እርምጃ እንደ መሰረት የተጠቀመበትን ሪፓርት፤ <u>እና</u>
- ከ LEA ጋር ከጠየቀው ወይም ከለከለው እርምጃ ጋር ተዛማጅ የሆኑ የሌሎች ሁኔታዎች ዝርዝር።

ከላይ የተዘረዘረውን መረጃ ማቅረብ LEA የእርስዎ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ በቂ እንዳልሆነ ከመግለፅ አያግደውም።

**በሂደት ላይ ላለ አቤቱታ የሌላ ወገን ምላሽ**

በክፍል ***በሂደት ላይ ላለ አቤቱታ የLEA ምላሽ*** ከተገለጸው በስተቀር፣ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ የሚቀበል አካል፣ አቤቱታውን በተቀበለ በአስር (10) ቀናት ውስጥ፣ በተለይም በአቤቱታ ውስጥ ለተነሳውን ጉዳይ የሚመልስ ምለሽ መስጠት ይገባዋል።

## ሞዴል ቅጾች

### 34 CFR §300.509

እርስዎ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ለማስገባት እንዲሁም እርስዎ እና ሌላኛው ወገን የግዛት አቤቱታ ለማስገባት ያግዛችሁ ዘንድ OSSE ሞዴል ቅፆችን አዘጋጅቷል፤ ሆኖም ግን፣ OSSEም ሆነ LEA እነኝህን ሞዴል ቅፆች እንድትጠቀሙ ይፈልግ ይሆናል። እንደ እውነቱ ከሆነ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታን ወይም የግዛት አቤቱታን ለማስገባት ቅፆቹ አስፈላጊውን መረጃ እስካካተቱ ድረስ ይህንን ቅፅ እና ሌሎች ተገቢ ቅፆችን መጠቀም ይችላሉ።

## *ድርድር*

## 34 CFR §300.506

እርስዎ እና LEA በ IDEA ክፍል B ስር ማንኛውንም ጉዳይ በተመለከተ ያልተስማማችሁበትን ጉዳዮች ለመፍታት ያስችላችሁ ዘንድ ድርድር መከናወን ይገባዋል፣ ይህም በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ከማስገባታችሁ በፊት ያለ ጉዳይን ይጨምራል። ስለሆነም፣ እርስዎ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ችሎትን ለመጠየቅ አቤቱታ ቢያስገቡም ወይም ባያስገቡም ድርድር በIDEA ክፍል B ስር የሚኖሩ ግጭቶችን ለመፍታት ይከናወናል።

### *መስፈርቶች*

አካሄዶቹ የድርድሩን ሂደት ማረጋገጥ ይገባቸዋል:-

- በእርስዎ ወገን እና በLEA ወገን በፈቃደኝነት የሚከናወን ነው፤
- በሂደት ላይ ላለ አቤቱታ የእርስዎን መብት ለመካድ ወይም ለማዘግየት አገልግሎት አይውልም፣ ወይም በIDEA ክፍል B ስር የተሰጡን ማንኛውንም ሌሎች መብቶች አይከለክልም፤ እና
- የሚከናወነው ብቃት ባለው እና ገለልተኛ በሆነ እና ውጤታማ በሆኑ የድርድር ቴክኒኮች በሰለጠነ አደራዳሪ ነው።

LEA ወላጆች እና ትምህርት ቤቶች የድርድር ሂደቱን እንዳይጠቀሙ የሚያደርጉ አካሄዶችን በማዘጋጀት ሊያቀርብ ይችላል፣ ይህም ፍላጎት ከሌለው አካል ጋር ፣ ለእርስዎ አመቺ በሆነ ቦታ እና ሰዓት የመገናኘት እድል ሊሆን ይችላል:-

- አግባብ ካለው አማራጭ የግጭት ፈቺ አካል ጋር በኮንትራት ውስጥ ያለ፣ ወይም የወላጅ ስልጠና እና መረጃ ማዕከል ወይም በኮሎምቢያ አውራጃ ውስጥ ለወላጆች የተዘጋጀ የወላጆች መረጃ ሃብት ማዕከል፤ እና
- የድርድርን ሂደት ጥቅሞች ለእርስዎ የሚያብራራ እና እርስዎን የሚያበረታታ።

OSSE ብቃት ያላቸውን እንዲሁም ከልዩ ትምህርት አቅርቦት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ህግጋት እና ደንቦች በሚገባ የሚያውቁ አደራዳሪዎች ዝርዝር ሊኖረው ይገባል። OSSE አደራዳሪዎችን ተከታታይ ባልሆነ፣ ሁሉንም በሚያዳርስ መልኩ፣ ወይም ያለ አንዳች መድልዎ መምረጥ ይገባዋል። OSSE የድርድሩን ሂደት ዋጋ የመሸፈን ሃላፊነት አለበት፣ ይህም የስብሰባዎችን ዋጋዎች ይጨምራል። በድርድር ሂደት ውስጥ እያንዳንዱ ስብሰባ ጊዜውን በጠበቀ መልኩ የጊዜ ሰሌዳ ሊያዝለት ይገባል እንዲሁም ለእርስዎ እና LEA አመቺ በሆነ ስፍራ መከናወን አለበት።

እርስዎ እና LEA በድርድር ሂደት ግጭት መፍታት ከቻላችሁ፣ ሁለቱም አካላት መፍትሄውን በሚዘረዝር በህግ ለሚገዛ ስምምነት መግዛት ይገባቸዋል:-

- በድርድር ሂደት ውስጥ የተከሰቱ ሁሉም ውይይቶች ሚስጥራዊ ሆነው ይቆያሉ እና በማንኛውም ተከታይ የአቤቱታ መስሚያ ሂደት ወይም የሲቪል አካሄድ (የፍርድ ቤት ጉዳይ) ውስጥ እንደ ማስረጃ ሊያገለግሉ አይችሉም፤ እና
- በእርስዎ እና LEAን ለመወሰን ስልጣን ባለው የ LEA ተወካይ የተፈረመ መሆን አለበት እና።

በፅሁፍ የቀረበ፣ የተፈረመ የድርድር ስምምነት በማንኛውም ተወዳዳሪ ስልጣን ባለው የግዛት ፍርድ ቤት (በግዛት ህግ ስር ያለ እንደዚህ አይነት ጉዳዮችን የሚመለት ፍርድ ቤት) ወይም በዩናይትድ ስቴትስ አውራጃ ፍርድ ቤት ተፈፃሚ ይሆናል።

በድርድር ሂደቱ ውስጥ የተደረጉ ውይይቶች ሚስጥራዊ መሆን አለባቸው። ወደፊት በሚደረጉ በማንኛውም አይነት የችሎት ሂደት ወይም በማንኛውም ፍርድ ቤት የሲቪል አካሄዶች ውስጥ አልያም ደግሞ በIDEA ክፍል B ስር እገዛ በሚቀበለው ግዛት ውስጥ ያለ የግዛት ፍርድ ቤት ውስጥ እንደ ማስረጃ በአገልግሎት ላይ ሊውሉ አይችሉም።

### *የአደራዳሪው/ዋ ገለልተኛነት*

አደራዳሪው/ዋ:-

- በእርስዎ ልጅ ትምህርት ወይም እንክብካቤ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ የOSSE ወይም LEA ተቀጣሪ መሆን አለባቸውም፤ እና
- ከአደራዳሪው ዓላማ ጋር ግላዊ ወይምሞያዊ ግጭቶች ሊኖረው/ራት አይገባም።

ለአደራዳሪነት ብቁ የሚሆን/የምትሆን ሰው የOSSE ተቀጣሪ መሆን የሌለበት ዋናው ምክንያት እሱ ወይም እሷ እንደ አደራዳሪ ለማገልገል የሚከፈላቸው በOSSE በመሆኑ ነው።

***መፍትሄ መስጫ ሂደት***

## 34 CFR §300.510 እና 5E DCMR §§3030.5, 3030.6, 3030.9, እና 3030.10

***መፍትሄ መስጫ ስብሰባ***

በሂደት ላይ ያለ አቤቱታን ማሳወቂያን በተቀበሉ በአስራ አምስት (15) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ እና በሂደት ላይ ያለው አቤቱታ መሰማት ከመጀመሩ በፊት፣ የተሳተፈው LEA ከእርስዎ ጋር እና ስለ እርስዎ አቤቱታ እውነታዎች የተለየ ዕውቀት ካላቸው የIEP ቡድን ተዛማጅ አባል ወይም አባላት ጋር ስብሰባ ማከናወን ይገባዋል። ስብሰባው፡-

- LEAን በመወከል ውሳኔ የመወሰን ስልጣን ያለው የ LEA ተወካይን ማካተት ይገባዋል፤ <u>እና</u>
- እርስዎ ጠበቃ ካላስከተሉ በስተቀር የ LEAን ጠበቃ ላያካትት ይችላል።

እርስዎ እና LEA ስብሰባውን የሚሳተፉትን ተዛማጅ የIEP ቡድን አባላት ትወስናላችሁ። የስብሰባው ዓላማ የእርስዎን በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ፣ እና አቤቱታው ስለተመሰረተበት እውነታዎች ለመወያየት ነው፣ ስለዚህ LEA ግጭቱን ለመፍታት እድል አለው።

የሚከተሉት ከሆነ የመፍትሄ መስጫ ስብሰባው አያስፈልግም፡-

- እርስዎ እና LEA ስብሰባውን ለማንሳት በፅሁፍ ከተስማማችሁ፤ <u>ወይም</u>
- ***ድርድር*** በሚለው ክፍል ስር እንደተዘረዘረው እርስዎ እና LEA የድርድር ሂደትን ለመጠቀም ከተስማማችሁ።

***የመፍትሄ መስጫ ጊዜ***

በሂደት ላይ ያለውን አቤቱታ በተቀበለ (በመፍትሄ መስጫ ሂሰቱ ጊዜ ውስጥ) በሰላሳ (30) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ LEA በሂደት ላይ ያለውን አቤቱታ በእርስዎ እርካታ ካልፈታ፣ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ መስሚያ ችሎት ሊከሰት ይችላል።

በመፍትሄ መስጫ ጊዜ ሰላሳ (30) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ማብቂያ ላይ በሂደት ላይ ላለ አቤቱታ የመጨረሻ ውሳኔ መስጫ የአርባ አምስት (45) የቀን መቁጠሪያ ቀናት የጊዜ ገደብ ይጀምራል፣ ከዚህ በታች እንደተዘረዘረው የሰላሳ (30) የቀን መቁጠሪያ ቀናትን ለማስተካከል ከሚደረጉ የተወሰኑ ልዩነቶች በስተቀር።

እርስዎ እና LEA ሁለታችሁም የመፍትሄ መስጫ ሂሰቱን ለማንሳት የተስማማችሁ እንደሆነ ወይም ድርድር ለመጠቀም ተስማምታችሁ ካልሆነ በስተቀር፣ በመፍትሄ መስጫ ስብሰባ ላይ ሳይሳተፉ ከቀሩ፣ ስብሰባው እስኪከናወን ድረስ የአቤቱታ ሰሚ መኮንኑ ትዕዛዝ የመፍትሄ መስጫውን ሂደት የጊዜ ሰሌዳ ማዘግየቱን ለመቀጠል LEA ሊጠይቅ ይችላል። ማንኛውም እንዲህ ያለ ጥያቄ LEA ከወላጆች ጋር የመፍትሄ መስጫ ስብሰባ ለማከናወን የወሰዳቸውን ማንኛውንም ምክንያታዊ እርምጃዎች ማስረጃ ያካተተ መሆን ይገባዋል። ምክንያታዊ እርምጃዎቹ ከዚህ በታች እንደተዘረዘሩት መሰናዳት አለባቸው። ከዚያም እርስዎ ለጥያቄዎቹ መልስ የመስጠት እና የአቤቱታ ሰሚው መኮንኑ ጥያቄው ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ተዛማጅ ማስረጃዎችን የማስገባት እድል ይኖርዎታል።

በተጨማሪም፣ ምክንያታዊ የሆነ ጥረት ካደረጉ በኋላ እና እንዲህ ሀሉ ጥረቶችን ካሰናዱ በኋላ፣ LEA በመፍትሄ መስጫ ስብሰባው ላይ የእርስዎን ተሳትፎ አያገኝም፣ LEA ምን አልባት፣ በመፍትሄ መስጫ ጊዜው በሰላሳ (30) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ማብቂያ ላይ፣ አቤቱታ ሰሚው መኮንን የእርስዎን በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ውሳኔ እንዲሰጥበት ይጠይቅ ይሆናል። LEA ጊዜውን ለማራዘም ካቀረበው ጥያቄ ጋር፣ ማንኛውም የእርስዎን በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ለማሻር የሚደረግ ጥያቄ የLEA ከወላጆች ጋር የመፍትሄ መስጫ ስምምነት ለማከናወን ያደረጋቸውን ምክንያታዊ እርምጃዎች የሚያሳይ ማስረጃን ማካተት ይገባዋል። ምክንያታዊ አርምጃዎቹ ከዚህ በታች እንደተገለፀው መሰናዳት አለባቸው። በድጋሚ፣ ለጥያቄው እና ተዛማጅ ማስረጃዎች የአቤቱታ ሰሚው መኮንን ጥያቄውን ከመመልከቱ በፊት የመመለስ እድል ይኖረዋል።

የእነኝህን ጥረቶች ሰነድ የLEA ሙከራዎችን የጋራ ስምምነት ላይ በተደረሰበት ጊዜ እና ሰዓት ሪኮርዱን ማካተት ያለበት ሲሆን እንደሚከተለው ይሆናል፡-

- የተደረጉ ወይም የተሞከሩ የስልክ ጥሪዎች ዝርዝር እና የአነኛ ጥሪዎች ውጤቶች፤
- ለእርስዎ የተላኩ የመልዕክት ልውውጦች ቅጂ እና ማንኛውም የተቀበሉዋቸው ምላሾች፤ <u>እና</u>
- ወደ ቤትዎ የተደረጉ ዝርዝር ጉብኝቶች ሰነዶች ወይም የቅጥርዎ ቦታ እና የጉብኝቶቹ ውጤቶች።

LEA በሂደት ላይ ያለ አቤቱታን ማሳወቂያ በተቀበለ በአስራ አምስት (15) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የመፍትሄ መስጫ ስብሰባ ማከናወን ካልቻለ ወይም በመፍትሄ መስጫ ስብሰባ ውስጥ ለመሳተፍ ከተሳነው፣ የአቤቱታ ሰሚ መኮንኑን የአርባ አምስት (45) የቀን መቁጠሪያ ቀናቱን በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ መስሚያ የጊዜ ሰሌዳን እንዲጀምር መጠየቅ ይችላሉ።

***ወደ ሰላሳ (30) የቀን መቁጠሪያ ቀን መፍትሄ መስጫ ጊዜ ማስተካከያዎች***

እርስዎ እና LEA የመፍትሄ መስጫ ስብሰባውን ለማንሳት በፅሁፍ ከተስማማችሁ፣ ከዚያ በሂደት ላይ ላለው አቤቱታ የአርባ አምስት (45) ቀናት የቀን መቁጠሪያ ቀን የጊዜ ሰሌዳ በማግስቱ ይጀምራል። ድርድሩ ወይም የመፍትሄ መስጫ ስብሰባው ከጀመረ በኋላ እና ከሰላሳ (30) የቀን መቁጠሪያ ቀን የመፍትሄ ጊዜ ከማለቁ በፊት እርስዎ እና LEA ምንም ስምምነት እንደማይሆን ከተስማማችሁ፣ በሂደት ላይ ያለው አቤቱታ የአርባ አምስት (45) የቀን መቁጠሪያ ቀናት የጊዜ ሰሌዳ በሚቀጥለው ቀን ይጀምራል።

እርስወፐ እና LEA የድርድር ሂደቱን ለመጠቀም ከተስማማችሁ ሆኖም ስምምነት ላይ ካልደረሳችሁ፣ በሰላሳኛው (30) የቀን መቁጠሪያ ቀን የመፍትሄ ጊዜ መጨረሻ፣ ሁለቱም አካላት መቀጠላቸውን በፅሁፍ በመግለፅ ከተስማሙ የድርድር ሂደቱ ስምምነት ላይ እስኪደረስ ድረስ ድርድሩ ይቀጥላል። ሆኖም ግን፣ እርስዎ ወይም LEA በዚህ የመቀጠል ጊዜ ውስጥ ከድርድር ሂደቱ ከወጣችሁ፣ በሂደት ላይ ያለው አቤቱታ የአርባ አምስት (45) የቀን መቁጠሪያ ቀናት የጊዜ ሰሌዳ በሚቀጥለው ቀን ይጀምራል።

በፅሁፍ የቀረበ የስምምነት መፈፀሚያ

የግጭት መፍትሄ ወደ መፍትሄ መስጫ ስብሰባ ከደረሰ፣ እርስዎ እና LEA በህግ ወደሚገዛ ስምምነት መግባት አለባችሁ እርሱም፡-

- በእርስዎ እና LEAን ለመወከል ስልጣን ባለው የ LEA ባለስልጣን መፈረም አለበት፤ እና
- በማንኛውም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በስራ ላይ የሚውል ይሆናል (እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ የመመልከት ስልጣን ያለው የግዛት ፍርድ ቤት) ወይም በዩናይትድ ስቴትስ አውራጃ ፍርድ ቤት።

**የስምምነት ክለሳ ጊዜ**

እርስዎ ወይም LEA በመፍትሄ መስጫ ስብሰባ ውጤት መሰረት ስምምነት ላይ ከደረሳችሁ፣ በከፊልም ቢሆን (እርስዎ ወይም LEA) ስምምነቱን እርስዎ እና LEA በፈረማችሁ በሶስት (3) የስራ ቀናት ውስጥ መሰረዝ ትችላላችሁ። ስምምነቱን የሰረዘ አካል ለሌሎቹ ለሁሉም አካላት በፅሁፍ የቀረበ ማሳወቂያ ማቅረብ ይገባዋል።

# በሂደት ላይ ያሉ አቤቱታዎች ችሎት

## ገለልተኛ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ መስሚያ ችሎት

### 34 CFR §300.511

በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ በሚገባበት በማንኛውም ሰዓት፣ እርስዎ ወይም LEA በግጭቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆናችሁት ገለልተኛ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ሰሚ ችሎት የማግኘት እድል ሊኖራችሁ ይገባል። OSSE በሂደት ላይ ያለ አቤቱታን የማጠቃለል ሃላፊነት አለበት።

**ገለልተኛ አቤቱታ ሰሚ መኮንን**

ቢያንስ፣ አቤቱታ ሰሚ መኮንኑ፡-

- ትምህርት ወይም እንክብካቤ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ የOSSE ወይም LEA ተቀጣሪ መሆን አለባቸውም፤ ሆኖም ግን ለአደራዳሪነት ብቁ የሚሆን/የምትሆን ሰው የOSSE ተቀጣሪ መሆን የሌለበት ዋናው ምክንያት እሱ ወይም እሷ እንደ አቤቱታ ሰሚ መኮንን ለማገልገል የሚከፈላቸው በOSSE በመሆኑ ነው፤
- ከአቤቱታ ሰሚ መኮንኑ ዓላማ ጋር ግላዊ ወይምሞያዊ ግጭቶች ሊኖረው/ራት አይገባም፤
- በቂ እውቀት ያለው እና ስለ IDEA አንቀፆች እና IDEAን በተመለከተ የፌደራል ስለ ግዛት ደንቦች የሚረዳ መሆን ይገባዋል እንዲሁም የIDEA በፌደራል እና በግዛት ፍርድ ቤቶች ያለውን ህጋዊ ፍቺን በሚገባ የሚያውቅ መሆን አለበት፤ እና
- አቤቱታ መስማትን ለማከናወን እውቀት እና ችሎታ ያለው፣ እና ውሳኔዎችን ማሳለፍ እና አግባብ ባለው ህጋዊ ተግባራት መሰረት በማድረግ መፃፍ የሚችል መሆን ይገባዋል።

OSSE እንደ አቤቱታ ሰሚ መኮንን ሆነው ያገለገሉን ሰዎች ስም ዝርዝር እና ብቃታቸውን የሚገልፅ መግለጫን በማካተት ማስቀመጥ ይገባዋል።

**በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ርዕሰ ጉዳይ**

በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ እንዲሰማላቸው ችሎት የሚጠይቁት ሁለቱ አካላት (እርስዎ ወይም LEA) በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ውስጥ መፍትሄ ያላገኙ ጉዳዮችን ሌላኛው ወገን ካልተስማማ በስተቀር በሂደት ላይ ባለ አቤቱታ መስሚያ ችሎት ውስጥ ላያነሱ ይችላሉ

አቤቱታ መስሚያ ችሎትን የመጠየቂያ የጊዜ ገደብ

እርስዎ ወይም LEA በአቤቱታው ውስጥ መፍትሄ የተሰጣቸውን ጉዳዮች ባወቃችሁ በሁለት (2) ዓመታት ጊዜ ውስጥ እርስዎ ወይም LEA በሂደት ላይ ላለ አቤቱታ ገለልተኛ የሆነ ሰሚ ችሎት መጠየቅ አለባችሁ።

### ለጊዜ ገደቡ ልዩ የሆኑ ነገሮች

በሚከተሉት ምክንያቶች በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ማስገባት ካልቻሉ ከላይ የተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ በእርስዎ ላይ በተግባር አይውልም፡-

በተለይም LEA ችግሩን እንደፈታ ወይም እርስዎ በአቤቱታ ውስጥ ያካተቱዋቸውን ጉዳዮች አሳስቶ ሊያቀርብ ይችላል፤ <u>ወይም</u>

- LEA በIDEA ክፍል B መሰረት ለእርስዎ ሊሰጥዎ የሚያስፈልገውን መረጃን በሚያዘገይ ጊዜ።

## የችሎት መብቶች

## 34 CFR §300.512 እና 5E DCMR §3029.5

በሂደት ላይ ባለ አቤቱታ እራስዎን ለመወከል መብት አለዎ። በተጨማሪም፣ ማንኛውም በሂደት ላይ ባለ ችሎት (ከዲሲፒሊን አካሄዶች ጋር ያለ ችሎትንም ጨምሮ) የሚከተሉትን የማድረግ መብት አለው፡-

- በጠበቃ እና/ወይም አካል ጉዳተኛ ልጆች ላይ ያሉ ችግሮችን በሚመለከት እውቀት ባለው ወይም ስልጠና በወሰደ ሰው ሊታጀብ እና ሊመከር ይችላል፤
- በችሎት ውስጥ በጠበቃው ሊወከል ይችላል፤
- ማስረጃ ማቅረብ እና ምስክሮችን መጋፈጥ፣ መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ እና እንዲቀርቡ ማድረግ፤
- ለአካላቱ ቢያንስ ከችሎቱ አምስት (5) የስራ ቀናት በፊት ያልተገለጸን ማንኛውንም አይነት ማስረጃ መቅረብን መከልከል፤
- የችሎቱን በፅሁፍ የተዘጋጀ፣ ወይም፣ በእርስዎ ምርጫ፣ የቃል በቃል ቅርጸተ ድምፅ ማግኘት፤ <u>እና</u>
- በፅሁፍ የቀረበ፣ ወይም፣ በእርስዎ አማራጭ፣ የእውነታዎች እና ውሳኔዎች ኤሌክትሮኒክ ግኝነቶች።

### ተጨማሪ መረጃዎችን መግለፅ

ከአቤቱታ መስሚያው ችሎት ቀን ቢያንስ አምስት (5) የስራ ቀናት ቀደም ብሎ፣ እርስዎ ወይም LEA በዚያ ቀን በችሎቱ ላይ እርስዎ ወይም LEA ለመጠቀም የሚሞሉትን ግምገማዎች እና በግምገማዎቹ ላይ መሰረት ያደረጉ ምክሮችን ማሳወቅ ይገባችኋል።

የአቤቱታ ሰሚ መኮንን ከሌላኛው ወገን ስምምነት ውጭ በችሎቱ ላይ ማንኛውንም ከዚህ በላይ ያለውን  መስፈርት ያላሟላ አካል ሃሳቡን ከመግለፅ ሊከለክል ይችላል።

በተጨማሪም፣ በጠበቃ የሚወከሉ ከሆነ፣ ጠበቃዎ ማንኛውንም እሱ ወይም እሷ የሚያውቀውን/የምታውቀውን የፋይናንስ ፍላጎት መግለፅ ይገባቸዋል፣ በአቤቱታ መስሚያ ሂደት ውስጥ የህዝብ ባልሆነ አቅራቢ በአቤቱታው ውስጥ እንደ ጉዳይ ሊሆን የሚችል ነገርን መግለፅ አለባቸው።

### የወላጆች የችሎት መብቶች

የሚከተሉትን ለማከናወን መብት አለዎ፡-

- ልጁ እንዲቀርብ ማድረግ፤
- ችሎቱ ለህዝብ ክፍት እንዲሆን ማድረግ፤ <u>እና</u>
- ያለምንም ክፍያ የችሎቱን የተቀረፀ ድምፅ ፣ የእውነታዎችን እና የውሳኔ ውጤቶችን ማግኘት ይችላሉ።

## የችሎት ውሳኔዎች

## 34 CFR §300.513

### የአቤቱታ ሰሚው መኮንን ውሳኔ

ልጅዎ ነፃ እና ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) ያገኝ ወይም አያገኝ ለመወሰን ከFAPE ጋር በቀጥታ ተዛማጅ በሆኑ ማስረጃዎች እና መከራከሪያ ነጥቦች ላይ መሰረት በማድረግ የአቤቱታ ሰሚ መኮንን ውሳኔዎችን ያሳልፋል።

አካሄዶችን በሚጥሱ ጉዳዮች ላይ (እንደ «ያልተሟላ IEP ቡድን»)፣ ላሉት አቤቱታ ሰሚ መኮንን በሚከተሉት የአካሄድ ጥሰቶች ሳቢያ ብቻ ልጅዎ FAPE አያገኝም፡-

- ከFAPE ጋር በልጅዎ መብት ዙሪያ ጣልቃ ከተገባ፤
- የFAPE አካሄዶች በተመለከተ በዋነኛነት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ጣልቃ የሚገባ ከሆነ፤ <u>ወይም</u>
- ልጅዎ ላይ የትምህርት ጥቅማ ጥቅም ችግር የሚያስከትል ከሆነ።

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሁኔታዎች ማናቸውም ቢሆኑ የአቤቱታ ሰሚ መኮንኑ በ IDEA ክፍል B ስር ካሉት የፌደራል ደንቦች የአካሄድ መጠበቂያዎች ክፍል ውስጥ ላሉት መስፈርቶች ተግዥ እንዲሆን LEAን ከማዘዝ ያግደዋል ተብሎ ሊተረጎም አይችልም (34 CFR §§300.500 እስከ 300.536)።

**በሂደት ላይ ላለ ችሎት የተለየ ጥያቄ**

በ IDEA ክፍል B ስር ካሉት የፌደራል ደንቦች የአካሄድ መጠበቂያዎች ክፍል ውስጥ (34 CFR §§300.500 እስከ 300.536) እርስዎን ከዚህ በፊት ከገባው የተለየ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ የተለየ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ከማስገባት እንደሚከለክልዎ ሊተረጎም የሚችል ምንም ነገር የለም ።

***ለመማክርት ፓነል እና በአጠቃላይ ለህዝቡ የሚቀርቡ ግኝቶች እና ውሳኔዎች***

ማንኛውንም በግል የሚገኝ መረጃን ከሰረዙ በኋላ፣ OSSE የሚከተሉትን ማድረግ ይገባዋል፡-

- በሂደት ላይ ያለውን ችሎት ግኝቶች እና ውሳኔዎች ለግዛት ልዩ የትምህርት መማክርት ፓነል ማቅረብ፤ <u>እና</u>
- እነኛን ግኝቶች እና ውሳኔዎች ህዝብ እንዲያገኛቸው ማድረግ።

## የይግባኝ ጥያቄዎች

### የውሳኔ መጨረሻ፤ ይግባኝ

**34 CFR §300.514**

በአቤቱታ መስሚያ ችሎት የተላለፈ ውሳኔ (የዲሲፒሊን እርምጃ ችሎትን ጨምሮ) የመጨረሻ ውሳኔ ነው፣ ሆኖም ማንኛውም በችሎቱ ተሳታፊ የሆነ አካል (እርስዎ ወይም LEA) ከዚህ በታች እንደተዘረዘረው፣ ሲቪል እርምጃ በማምጣው በውሳኔው ላይ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ።

### የችሎቶች የጊዜ ገደብ እና አመቺነት

**34 CFR §300.515 and 5E DCMR §§3030.11 and 3030.12**

OSSE የመፍትሄ መስጫ ስብሰባ የሰላሳ (30) የቀን መቁጠሪያ ቀን ካለፈ በኋላ <u>ወይም</u> ***በሰላሳ (30) የቀን መቁጠሪያ ቀን መፍትሄ የመስጫ ጊዜ ማስተካከያዎች*** ክፍል ስር እንደተጠቀሰው የማስተካከያ ጊዜው ካለፈ በኋላ ከአርባ አምስት (45) የቀን መቁጠሪያ ቀን ባልበለጠ ጊዜ መሆን እንደሚገባው የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት፡-

- በችሎቱ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እንደተወሰደ፤ <u>እና</u>
- የውሳኔው ቅጂ ለሁለቱም አካላት በፓስታ መላክ አለበት ወይም እንደ አማራጭ ሁሉም አካላት በሂደት ላይ ያለው አቤቱታ ቅጂ በኢሜይል አልያም በፋክስ ሜይል እንዲላክ ከተስማሙ በሁለቱ አማራጭ ሊላክ ይችላል።

አቤቱታ ሰሚ መኮንኑ ለሚታይ ጥሩ ምላሽ፣ ከአርባ አምስቱ (45) የቀን መቁጠሪያ ቀናት በተጨማሪ የተወሰነ የጊዜ ማራዘሚያ ሊሰጥ ይችላል ይህም ከላይ እንደተገለጸው ከሁለቱ አካላት በአንዱ ሲጠየቅ ነው።

እያንዳንዱ ችሎት ለእርስዎ እና ለልጅዎ አመቺ በሆነ ጊዜ እና ቦታ ላይ መከናወን ይገባዋል።

## ሲቪል እርምጃዎች፣ እርምጃዎቹን ለማስገባት የተሰጠውን የጊዜ ገደብ ጨምሮ

## 34 CFR §300.516

ማንኛውም አካል (እርስዎ ወይም LEA) በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ችሎት ላይ በተገኘው ውጤት እና ውሳኔ ያልተስማማ አካል (ከዲሲፒሊን አካሄዶች ጋር የተያያዘ ችሎትን ጨምሮ) በሂደት ላይ በነበረው ርዕስ ጋር በተያያዘ ወደ ሲቪል እርምጃ የማምጣት መብት አለው። እርምጃው ወደ ኮሎምቢያ አውራጃ ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ወይም እንዲህ አይነቱን ጉዳይ ወደ ሚያዩ የሌላ ግዛት ፍርድ ቤቶች) ወይም የግጭቱ መጠን ግምት ውስጥ ሳይገባ ለዩናይትድ ስቴትስ አውራጃ ፍርድ ቤት ሊመጣ ይችላል።

### የጊዜ ገደብ

ሁለቱም እርምጃውን አቤቱታ የሚያቀርቡት አካላት (እርስዎ ወይም LEA) ሲቪል እርምጃን ለማስገባት በአቤቱታ ሰሚ መኮንን ውሳኔው ከተሰጠ ቀን አንስቶ 90 የቀን መቁጠሪያ ቀናት አላቸው።

### ተጨማሪ አካሄዶች

በማንኛውም የሲቪል እርምጃ ውስጥ፣ ፍርድ ቤቱ፦

- የአስተዳደር አካሄዶችን ሰነዶች ይቀበላል፤
- በእርስዎ ወይም በ LEA ጥያቄ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ይሰማል፤ እና
- ውሳኔውን በአብዛኛው ማስረጃ መሰረት ያደርጋል እና ፍርድ ቤቱተ አግባብ ነው ብሎ ያመነበትን መፍትሄ ይሰጣል።

አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች ውስጥ፣ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ህጋዊ መፍትሄ የግል ትምህርት ቤት ክፍያ እና የትምህርት አገልግሎቶች ማካካሻዎችን ሊያጠቃልል ይችላል።

### የአውራጃ ፍርድ ቤቶች ስልጣን

የዩናይት ስቴትስ አውራጃ ፍርድ ቤቶች በIDEA ክፍል B ስር የሚመጡ እርምጃዎችን የመግዛት ስልጣን አለው ይህም በግጭት ውስጥ ያለውን መጠን ከግምት ሳያስገባ።

### የግንባታ ደንብ

በIDEA ክፍል B ስር በዩ.ኤስ ህገ መንግስት ስር፣ የ1990ውን አካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን አዋጅን፣ የ1973ቱን የማቋቋሚያ አዋጅ ርዕስ V(ክፍል 504)፣ ወይም ሌሎች የአካል ጉዳተኛ ልጆች መብቶችን የሚጠብቁ የፌደራል ህግጋት ውስጥ ያሉትን መብቶች፣ አካሄዶች፣ እና መፍትሄዎች አያግድም፣ ይህም በእነዚህ ህግጋት በIDEA ክፍል B ስር የሚገኙትን የመገላገያዎች ሲቪል እርምጃዎች ጥያቄን ከማስገባትዎ በፊት ከሆነ ብቻ፣ አንዱ አካል በIDEA ክፍል B ስር እርምጃን ካስገባ ከላይ የተገለጸው በሂደት ላይ ያለ አካሄዶችን እንደአስፈላጊነቱ በተመሳሳይ ሁኔታ መከናወን ይገባዋል። ይህ ማለት በሌሎች እርስ በእርስ በሚደጋገፉ ህግጋት ስር እንዲሁም በ IDEA ስር መፍትሄዎች ሊኖርዎ ይችላል፣ ሆኖም ግን በአጠቃላይ፣ በእነኛ በሌሎች ህግጋት ስር መፍትሄ ለማግኘት፣ በመጀመሪያ በ IDEA ያሉትን አስተዳደራዊ መፍትሄዎች መጠቀም ይገባል ( ለምሳሌ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ፤ የመፍትሄ አሰጣጥ ሂደት፣ የመፍትሄ አሰጣጥ ስብሰባን ጨምሮ፤ እና ገለልተኛ በሂደት ላያ ያለ አቤቱታ መስሚያ አካሄዶች) በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ከመሄድዎ በፊት የሚከናወን ነው።

## በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ እና ችሎቱ በሂደት ላይ ባለ ጊዜ የአንድ ልጅ ምደባ

## 34 CFR §300.518

ከዚህ በታች ***አካል ጉዳተኛ የሆኑ ልጆችን ዲሲፒሊን የማስያዝ አካሄዶች*** በሚለው ክፍል ስር ከተሰጠው በቀር፣ አንድ ጊዜ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ወደ ሌላኛው አካል ከተላከ፣ በመፍትሄ አሰጣጥ የጊዜ ሂደት ውስጥ፣ እና የማንኛውንም ገለልተኛ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ችሎት ወይም የፍርድ ቤት አካሄድ፣ እርስዎ እና OSSE ወይም LEA ካልተስማማችሁ በስተቀር፣ ልጅዎ አሁን ባለበት ወይም ባለችበት የትምህርት ምደባ ውስጥ መቆየት ይገባቸዋል።

በሂደት ላይ ያለው አቤቱታ የህዝብ ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ ለመግባት ማመልከቻን ያካተተ ከሆነ፣ በእርስዎ ስምምነት፣ ሁሉም እነኝህ አካሄዶች እስኪጠናቀቁ ድረስ ልጅዎ፣ በመደበኛ የህዝብ ትምህርት ቤት ፕሮግራም መመደብ አለበት።

በ IDEA ክፍል B ስር በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ከIDEA ክፍል C ወደ IDEA ክፍል B የሚሸጋገርን እና ከዚህ በኋላ ልጁ ሶስት ዓመት ስላለፈው ለክፍል C አገልግሎቶች ብቁ ያልሆነ ልጅን የመጀመሪያ አገልግሎቶች ማመልከቻዎችን ካካተተ፣ LEA ልጁ ሲቀበል የነበረውን የክፍል Cን አገልግሎቶች መስጠት አያስፈልገውም። ልጅዎ በ IDEA ክፍል B ስር ብቁ ከሆነ እና እርስዎም ለመጀመሪያ ጊዜ ልጁ ልዩ ትምህርትን እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን እንዲቀበል ፈቃደኛ ከሆኑ፣ ከዚያም የአካሄዶቹን ውጤቶች በማቆየት፣ LEA እነኛን በግጭት ውስጥ ያልሆኑ (ሁለታችሁም እርስዎ እና LEA የተስማማችሁባቸው) ልዩ የትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት ይገባዋል።

በ OSSE በሚከናወን በሂደት ላይ ባለ ችሎት የአቤቱታ ሰሚ መኮንን የምደባ ለውጥ አግባብ እንዳለው ከእርስዎ ጋር ከተስማማ፣ ምደባው አሁን እንዳለ የልጅዎ የትምህርት ምደባ መቆጠር አለበት ይህም ልጅዎ በማንኛውም ገለልተኛ የአቤቱታ ሂደት ችሎት ወይም የፍርድ ቤት አካሄድ ውሳኔን በመጠባበቅ ላይ እያለ የሚቆይበት ስፍራ መሆን ይገባዋል።

## የጠበቃ ክፍያዎች

## 34 CFR §300.517 እና 5E DCMR §3032.4

በ IDEA ክፍል B ስር በመጣ ማንኛውም እርምጃ እና አካሄድ፣ ፍርድ ቤቱ፣ ባለው ሚዛናዊ አስተዳደር፣ የሚረቱ ከሆነ (ካሸነፉ) እንደ እርስዎ ወጪ አካል በመቁጠር ምክንያታዊ የጠበቃ ክፍያን ሊሰጥ ይችላል።

በ IDEA ክፍል B ስር በመጣ ማንኛውም እርምጃ እና አካሄድ፣ ፍርድ ቤቱ፣ ባለው ሚዛናዊ አስተዳደር፣ ክርክሩን ለረታው LEA ወይም ለሌላ የህዝብ ኤጀንሲ፣ ወጭ ተቆጥሮ ምክንያታዊ የሆነ ክፍያን ፍርድ ቤቱ ይሰጣል ፣ ይህም የሚከፈለው በጠበቃዎ በኩል ሲሆን ጠበቃውም፦

- ፍርድ ቤቱ ውድቅ ሆኖ ያገኘውን፣ ምክንያታዊ ያልሆነ፣ ወይም መሰረት የሌለው አቤቱታ ወይም የፍርድ ቤት ጉዳይ አስገብቶ ከነበር፤ ወይም
- ክርክሩ ውድቅ ሆኖ ከተገኘ በኋላ ምክንያታዊ ባልሆነ መልኩ ወይም ያለምንም መሰረት ክርክሩን ከቀጠለ፤ ወይም
- በማንኛውም የ IDEA ክፍል B እርምጃ ወይም አካሄድ ስር ከመጣ፣ ፍርድ ቤቱ፣ ባለው ስልጣን አሁን የረታው LEA ወይም የህዝብ ኤጀንሲ ወጭዎች አካል በማሰብ ፣ አግባብ ያለው ክፍያን ይሰጣል፣ ይህም በእርስዎ ወይም በጠበቃው የሚሸፈን ሲሆን በሂደት ላይ ላለው አቤቱታ ችሎት የእርስዎ ጥያቄ ወይም ቀይቶም ለፍርድ ቤት የቀረበው ጥያቄ ትክክለኛ ላልሆነ ዓላማ ቀርቦ ከነበረ፣ ለመተንኮስ፣ ያልተገባ መዘግየትን ለማስከተል፣ አልያም ደግ ባልተገባ ሁኔታ የሂደቱን (የችሎቱን) ወጭ ለመጨመር ታስቦ ከነበር ጠበቃው ወጭውን ይከፍላል።

### የሚሸፈኑ ክፍያዎች

ፍርድ ቤቱ አግባብ ያለው ክፍያን ለጠበቃው እንዲከፈል ያደርጋል ይህም እንደሚከተለው ይሆናል፦

- ክፍያው ተግባሩ በተፈፀመበት ወይም አቤቱታው በተነሳበት በማህበረሰብ ውስጥ ባለው የዋጋ ተመን ላይ እንዲሁም በተሰጡት አገልግሎቶች ጥራት ላይ መሰረት ማድረግ ይገባዋል።
- ክፍያዎች በIDEA ክፍል B ስር ላሉ ክፍያዎች በፅሁፍ የተሰጠ አፈፃፀም ከቀረበ በኋላ ለሚከዋኑ አገልግሎቶች እርምጃ ወይም አካሄድ ክፍያ ለሰይሰጥ ወይም ተዛማጅ ወጭዎች ላይመለስ ይችላል፦

  ሀ. የሚሰጠው ክፍያ በፌደራል የሲቪል አካሄድ ደንቦች ቁጥር 68 ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል ወይም፣ በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ ችሎት በሚሆን ጊዜ፣ አካሄዱ ከመጀመሩ አስር (10) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ቀደም ብሎ በማንኛውም ጊዜ ሊሆን ይችላል፤

  ለ. የሚሰጠው ክፍያ በአስር (10) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ተቀባይነት ካላገኘ፤ እና

  ሐ. ፍርድ ቤቱ ወይም የአስተዳደር አቤቱታ ሰሚ መኮንንን በመጨረሻ የእርስዎ ነፃ መሆን ከማስፈፀሚያው ክፍያ ይልቅ ለእርስዎ መልካም እንዳልሆነ በሚያውቅ ጊዜ።

  ከእነኝህ ገደቦች ውጭ፣ የጠበቃ ወጭዎች ክፍያ እና ተዛማጅ ወጭዎች ክፍያ ሊከፈልዎ ይችላል፣ ይህም የሚሆነው እርስዎ ክርክሩን ከረቱ እና በዋነኛነትም የማስፈጸሚያ ክፍያን እንዳልተቀበሉ ሲረጋገጥ ነው።

- ከ IEP ቡድኖች ለአስተዳዳራዊ አካሄዶች ወይም የፍርድ ቤት እርምጃ ስብሰባ ሲኖርዎ ካልሆነ በቀር ከሌሎች ስብሰባዎች ጋር በተያያዘ ምንም አይነት ክፍያዎች አይፈፀሙም ።

የመፍትሄ መስጫ ስብሰባ፣ ***የመፍትሄ መስጫ ሂደት*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው፣ በአስተዳዳራዊ ችሎት ወይም ፍርድ ቤት እርምጃ ሳቢያ እንደሚከናወን ስብሰባ አይቆጠርም፣ እንዲሁም ለዚህ ጠበቃ ክፍያ አሰጣጥ ዓላማዎች እንደ አስተዳደራዊ ችሎ ወይም የፍርድ ቤት እርምጃ አይቆጠርም።

በIDEA ክፍል B ለሚሰጡ የጠበቃ ክፍያዎች ፍርድ ቤቱ፣ አግባብ ባለው መልኩ መጠኑን ይቀንሳል ፣ የሚከተሉትን የሚያገኝ ከሆነ ፍርድ ቤቱ፦

- እርስዎ ወይም የእርስዎ ጠበቃ፣ በእርምጃው ሂደት ወይም በአካሄድ ጊዜ፣ የግጭቱን የመጨረሻ መፍትሄ አግባብ ባልሆነ መልኩ ካዘገያችሁት፤
- እንዲከፈል ፈቃድ የተሰጠው የጠበቃ ክፍያዎች መጠን አግባብ በልሆነ መልኩ ተወስኖ ከሆነ እና በማህበረሰብ ውስጥ ለተመሳሳይ አገልግሎቶች፣ ተመሳሳይ ችሎታ፣ ዝና እና ልምድ ላላቸው ጠበቃዎች በሰዓት ከሚከፈለው የክፍያ መጠን ከበለጠ፤

- የእርምጃውን ሁኔታ እና አካሄድ ከግምት በማስገባት የባከነው ጊዜ እና ህጋዊ አገልግሎቶቹ ከልክ ያለፈ ከሆነ፣ ወይም
- እርስዎን የሚወክለው ጠበቃ ***በሂደት ላይ ያለ አቤቱታ*** በሚለው ክፍል ስር እንደተገለጸው በሂደት ላይ ያለውን አቤቱታ ጥያቄ ማሳወቂያ አግባብ ባለው መልኩ ለLEA መረጃ ሳይሰጥ ሲቀር።

ሆኖም ግን፣ ፍርድ ቤቱ OSSE ወይም LEA የመጨረሻውን መፍትሄ አሰጣጥ እርምጃ ወይም አካሄድ ያለ አግባብ እንዳዘገዩት ከደረሰበት አልያም ደግሞ በIDEA ክፍል B ስር የአካሄድ መጠበቂያዎች ጥሰቶች ተካሂዶ ከነበር ፍርድ ቤቱ ክፍያዎችን ላይቀንስ ይችላል።

ማንኛውም እርስዎ LEA የሚጠይቁት የጠበቃ ክፍያ፣ እርስዎ LEA በመቃወም ከተከራከሩ፣ የአቤቱታው ውሳኔ በተሰጠ ወይም እንዲህ ያሉ ክፍያዎችን የሚፈልጉ የአፈፃፀም ስምምነት በተላለፈ በአርባ አምስት (45) ውስጥ የክፍያ ጥያቄው መግባት አለበት። ይህንን ሳያከናውኑ መቅረት በ LEA ሂደቱን የማዘግየት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል።

## በአካል ጉዳተኛ ልጆች ላይ የዲሲፒሊን እርምጃ የመውሰድ አካሄዶች

**[ማስታወሻ፡-የኮሎምቢያ አውራጃ የህዝብ ትምህርት ቤት ( The District of Columbia Public Schools (DCPS)) አካል ጉዳተኛ ልጆች ላይ የዲሲፒሊን እርምጃን ለመውሰድ የተለያዩ አካሄዶችን በስራ ላይ አውሏል። ልጅዎ DCPS ትምህርት ቤቶች ወይም DCPS እንደ LEA እንዲያገለግል በተመረጡ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ከተመዘገበ/ች፣ በ IDEA የሚፈለጉ የ DCPS ዲሲፒሊን አካሄድ መጠበቂዎች ቅጂ ሊሰጥዎ ይገባል።]**

## የትምህርት ቤት ሰራተኛ ስልጣን

## 34 CFR §300.530

***የጉዳይ-በ-ጉዳይ ውሳኔዎች***

የትምህርት ቤት ሰራተኛ ማንኛውንም ልዩ ሁኔታዎች ጉዳይ-በ-ጉዳይ ላይ መሰረት በማድረግ ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል ፣ በሚከተሉት ከዲሲፒሊን፣ የተማሪዎችን ስነምግባር ከጣሰ አካል ጉዳተኛ ልጅ ጋር አግባብ ላለው ሁኔታ መስፈርቶች ጋር በተያያዘ የምደባ ለውጥ በሚወሰን ጊዜ እነኝህ ሁኔታዎች ከግምት ይገባሉ።

***አጠቃላይ***

እንዲህ ያለውን እርምጃ አካል ጉዳተኛ ባልሆኑ ልጆች ላይ ይወስዳሉ፣ የትምህርት ቤት ሰራተኛ፣ በተከታታይ **ከአስር (10) *የትምህርት ቀናት***፣ የተማሪዎችን ስነ ምግባር ኮድ የጣሰ/ች አካል ጉዳተኛ ልጅን አሁን ካለበት/ካለችበት ምደባ በማንሳት አግባብ ወዳለው ተዛማጅ ትምህርት ቤት፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ አቅርቦት ወደሚሰጥ ተቋም ሊያዘዋውር ይችላል/ትችላለች ወይም ደግሞ እግድ ሊሰጥ ይችላል። የትምህርት ቤት ሰራተኛ ተከታታይ **አስር (10) *የትምህርት ቀናት*** በተመሳሳይ የትምህርት ዓመት ውስጥ በተለያዩ ጊዜ ለተፈፀሙ የስነ ምግባር ግድፈቶች፣ እገዳዎቹ የምደባ ለውጥን እስካላመጡ ድረስ፣ በልጁ ላይ ተጨማሪ እግድ እንዲጣል ጫና መፍጠር ይችላል (***በዲሲፒሊን እርምጃ ምክንያት የተደረገ የምደባ ለውጥ*** በሚለው ንኡስ ርዕስ ስር ያሉትን ፍቺዎች ይመልከቱ)።

አካል ጉዳተኛ ልጅ አንድ ጊዜ አሁን ካለበት/ችበት ምደባ በተመሳሳይ ዓመት ውስጥ **ለአስር (10) *የትምህርት ቀናት*** ከታገደ/ች፣ በንኡስ ርዕስ ***አገልግሎቶች*** በሚለው ስር በሰፈረው መሰረት LEA በሚከተሉት በማናቸውም የትህርት ዓመት ውስጥ ባሉ የእግድ ቀናት አገልግሎቶችን መስጠት ይገባዋል።

***ተጨማሪ ስልጣን***

የተማሪዎችን የስነ ምግባር ኮድ የጣሰው የባህሪይ አይነት የልጁ/ቷ አካል ጉዳት መገለጫ ካልሆነ (***የመገለጫ መወሰኛ*** ክፍል ስር ያለውን ይመልከቱ*)* እና የዲሲፒሊን እርምጃው የቦታ ለውጥ ተከታታይ **አስር (10) *የትምህርት ቀናትን*** ካለፈ፣ ትምህርት ቤቱ ***አገልግሎቶች*** በሚለው ክፍል ስር እንደተገለፀው ለዚያ ልጅ አገልግሎቶችን ካላቀረበ በስተቀር የትምህርት ቤት ሰራተኛው በዚያ አካል ጉዳተኛ ልጅ ላይ አካል ጉዳተኛ ያልሆኑ ልጆች ላይ እንደሚወሰደው የዲሲፒሊን እርምጃ አካሄድ ተመሳሳይ አካሄድን በተግባር ያውላል።

***አገልግሎቶች***

የእርስዎ LEA ለሁለቱም ማለትም አካል ጉዳተኛ ለሆኑ እና አካል ጉዳተኛ ላልሆኑ እና አሁን ካለበት/ካለችበት ምደባ በተመሳሳይ ዓመት ውስጥ **ለአስር (10) *የትምህርት ቀናት ወይም ከዚያ ላነሰ ጊዜ*** ከትምህርት ቤት ለሚታገዱ ልጆች አገልግሎቶችን ሊሰጥ ይችላል፣ ሆኖም ግን መስጠት ላይጠበቅበት ይችላል። እንዲህ ያሉት አገልግሎቶች እንደሚሰጡ ለማወቅ የእርስዎን LEA ማነጋገር አለብዎ።

አሁን ካለበት/ችበት ምድብ **ከአስር (10) *የትምህርት ቀናት በላይ*** *የታገደ/ች አካል ጉዳኛ ለሆነ/ች ልጅ፣ ያሳየው/ችው ባህሪይ ከአካል ጉዳተኝነት መገለጫ ጋር ተያያዥነት የሌለው ከሆነ (**የመገለጫ መወሰኛን** ክፍልን ይመልከቱ)* ወይም በልዩ ሁኔታዎች የታገደ/ች ከሆነ (***ልዩ ሁኔታዎች*** የሚለውን ክፍል ይመልከቱ) እሱ ወይም እሷ የሚከተለውን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡-

1. የትምህርት አገልግሎቶችን መቀበሉን ይቀጥላል (አግባብ ያለው ነፃ የህዝብ ትምህርት (Free Appropriate Public Education (FAPE)) ያገኛል፣ ምንም እንኳን በሌላ ስፍራ ቢሆንም፣ ልጁ በአጠቃላይ የትምህርት ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ተሳትፎውን ለመቀጠል ያስችለዋል (ይህም ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ስፍራ ሊሆን ይችላል)፣ እና በልጁ IEP የተቀመጠውን ግብ ሂደት ከዳር ለማድረስ፤ <u>እና</u>

2. አግባብ ያለው፣ በተግባር ላይ የዋለ የባህሪይ ግምገማ እና የባህሪይ መሻሻል ጣልቃ ገብነት አገልግሎት እና ማሻሻያዎችን ይቀበላል፣ እነሱም ለጥሰት እና አላስፈላጊ ባህሪይ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት የተነደፉ ሲሆኑ በድጋሚ እንዳይከሰቱ ለመከላከል ነው።

አካል ጉዳተኛ ልጅ በተመሳሳይ የትምህርት ዓመት ውስጥ **ለአስር (10) *የትምህርት ቀናት*** አሁን ካለበት ምደባ ከታገደ በኋላ፣ እና አሁን ያለው እግድ በተከታታይ **ለአስር (10) *የትምህርት ቀናት* <u>ከሆነ</u>** ወይም ካነሰ **እና** እግዱ የምደባ ለውጥ ካልለሆነ (ከዚህ በታች ያለውን ፍቺ ይመልከቱ)፣ ***<u>ከዚያ</u>*** የትምህርት ቤት ሰራተኛው፣ ቢያንስ ከአንድ የልጁ አስተማሪ ጋር በመማከር፣ ልጁ በአጠቃላይ የትምህርት ስርዓተ ትምህርት ውስጥ መሳተፉን እንዲቀጥል ምን አይነት አገልግሎት እንደሚያስፈልግ ይወስናሉ፣ ምንም እንኳን በሌላ ስፍራ ቢሆንም፣ እንዲሁም በልጁ IEP የተቀመጠውን ግብ ሂደት ከዳር ለማድረስ እንዲችል ለማድረግ ነው።

እገዳው የቦታ ለውጥ ከሆነ (***በዲሲፕሊን እርምጃ ምክንያት የተደረገ የምደባ ለውጥ*** የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ)፣ ምንም እንኳን በሌላ ስፍራ ቢሆንም የልጁ IEP ቡድን ልጁ በአጠቃላይ የትምህርት ስርዓተ ትምህርት ውስጥ መሳተፉን እንዲቀጥል አግባብ ያላቸው አገልግሎቶችን ይወስናል፣(ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ስፍራ ሊሆን ይችላል)፣ እንዲሁም በልጁ IEP የተቀመጠውን ግብ ሂደት ከዳር ለማድረስ እንዲችል ለማድረግ ነው።

***የመገለጫ መወሰኛ***

የትምህርት ቤት ስነ ምግባር ኮድን በመጣሱ ምክንያት አካል ጉዳተኛ ልጅ የቦታ ለውጥ ላይ የሚወሰን ማንኛውም ውሳኔ **በአስር (10) *የትምህርት ቀናት*** (**ለአስር (10) *ተከታታይ ቀናት*** ወይም ከዚያ ላነሰ እና የቦታ ለውጥ ላለውሆነ እግድ ከሚወሰን ውጭ ያለው) LEA፣ እርስዎ፣ እና ሌሎች ተዛማጅ የ IEP ቡድን አባላት (በእርስዎ እና LEA እንደሚወሰነው) በተማሪው ፋይል ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ተዛማጅ መረጃ መገምገም ይገባችኋል፣ የልጁን IEP ጨምሮ፣ ማንኛውንም የአስተማሪ እይታዎች፣ እና ማንኛውንም እናንተ ለመወሰን የሚያስችላችሁን ተዛማጅ መረጃ ማየት ይገባችኋል፡-

1. በጥያቄ ውስጥ ያለው ፀባይ የተከሰተው፣ በዋነኛነት ከልጁ/ልጅቷ አካል ጉዳተኝነት ጋር ግንኙነት ባለው መልኩ ከሆነ፤ <u>ወይም</u>

2. በጥያቄ ውስጥ ያለው ፀባይ IEP በስራ ላይ ለማዋል የ LEA ቀጥተኛ ውድቀት ከሆነ።

LEA፣ እርስዎ እና ሌላ የልጁ ተዛማጅ IEP ቡድን አባል ከሁለቱ አንዱ ሁኔታ ተከስተዋል ብለው ከወሰኑ፣ የታየው ፀባይ የልጁ/ቷ አካል ጉዳተኝነት መገለጫ መሆን አለበት ብለው ይወስናሉ።

LEA፣ እርስዎ እና ሌላ የልጁ ተዛማጅ IEP ቡድን አባል በጥያቄ ውስጥ ያለው ፀባይ IEP በስራ ላይ ለማዋል የ LEA ቀጥተኛ ውድቀት ውጤት ከሆነ፣ ለችግሮቹ መፍትሄ ለመፈለግ LEA ፈጣን እርምጃን መውሰድ ይገባዋል።

***ባህሪይው የልጁ/ልጅቷ አካል ጉዳተኝን መገለጫ እንደሆነ መወሰን***

LEA፣ እርስዎ እና ሌላ የልጁ ተዛማጅ IEP ቡድን አባል በልጁ/ቷ ላይ የታየው ፀባይ የአካል ጉዳተኝነት መገለጫ ነው ብላችሁ ከወሰናችሁ፣ የIEP ቡድን የሚከተሉት አንዱን ማድረግ አለበት፡-

1. ምደባን ያስቀየረው ባህሪይ ከመከሰቱ በፊት LEA ቀድውኑ የተግባራዊ የባህሪይ ግምገማን አካሂዶ ለልጁ የባህሪይ መፍትሄ አሰጣጥ ዕቅድን በተግባር ላይ ካላዋለ በስተቀር IEP የተግባራዊ የባህሪይ ግምገማን ማካሄድ አለበት፤ <u>ወይም</u>

2. የባህሪይ መፍትሄ አሰጣጥ ዕቅድ ቀድሞውኑ የተዘጋጀ ከሆነ፣ ለባህሪየው መፍትሄ ለመስጠት ቀድሞ የተዘጋጀውን እንደ አስፈላጊነቱ፣ ማሻሻል።

ከዚህ በታች ***በልዩ ሁኔታዎች*** ስር ከተገለፀው በስተቀር፣ እርስዎ እና LEA እንደ የባህሪይ መፍትሄ ዕቅድ አሰጣጥ ማሻሻያ ለማየት ካልተስማማችሁ በቀር LEA ልጅዎን ከታገደበት የምደባ ቦታ መመለስ አለበት።

**ልዩ ሁኔታዎች**

ባህሪይው የልጅዎ የአካል ጉዳተንነት መገለጫ ሆነም አልሆነም፣ የትምህርት ቤት ሰራተኛ ልጁን ወደ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ስፍራ እንዲሄድ ያድርገዋል (ይህም የሚወሰነው በልጁ IEP ነው) ልጅዎ በሚከተለው ሁኔታ ካለ ከአርባ አምስት (45) የትምህርት ቀናት ባልበለጠ ፦

1. መሳሪያ ከያዘ (ፍቺውን ከዚህ በታች ይመልከቱ) ወይም ወደ ትምህርት ቤት መሳሪያ ይዞ መከጣ፣ ወይም በትምህርት ቤት ጊቢ ውስጥ መሳሪያ ይዞ ከተገኘ፣ ወይም በግዛት የትምህርት ኤጀንሲ ወይም LEA በህጋዊ ባለስልጣን ስር ባለ የትምህርት ቤት ተግባር፤
2. በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ጊቢ ውስጥ ወይም በግዛት የትምህርት ኤጀንሲ ወይም LEA በህጋዊ ባለስልጣን ስር ባለ የትምህርት ቤት ተግባር ሆን ብሎ ህገ ወጥ መድሃኒት/እፅ ይዞ ሲገኝ፣ (ከዚህ በታች ፍቺውን ይመልከቱ)፣ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበትን ንጥረ ነገር (ፍቺውን ከዚህ በታች ይመልከቱ) ከሸጠ ወይም ካዋዋለ፤ <u>ወይም</u>
3. በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ጊቢ ውስጥ ወይም በግዛት የትምህርት ኤጀንሲ ወይም LEA በህጋዊ ባለስልጣን ስር ባለ የትምህርት ቤት ተግባር በሌላ ሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ካደረሰ (ፍቺውን ከዚህ በታች ይመልከቱ)።

**ፍቺዎች**

*ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች* ማለት መድሃኒት ወይም ቁጥጥር በሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች አዋጅ (21 U.S.C. 812(c)) ሰንጠረዥ I, II, III, IV, ወይም V ክፍል 202 (c) ስር ተለይተው የተቀመጡት ሌሎች ዕፅ የሚባሉት ናቸው።

*ህገወጥ መድሃኒት* ማለት ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች ሲሆኑ፣ ሆኖም ግን ፈቃድ ባለው የጤና እንክብካቤ ባለሞያ ምክር ህጋዊ በሆነ መልኩ የሚወሰዱ ወይም በአገልግሎት ላይ የሚውሉ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮችን ወይም በሌላ በአዋጁ ስር ፈቃድ ባለው ህጋዊ ባለስልጣን ወይም በፌደራል ህግ ስር የሚወሰዱትን ወይም አገልግሎት ላይ የሚውሉትን ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ንጥረ ነገሮች አያካትትም።

*ከባድ የአካል ጉዳት* የሚለው ቃል ትርጉም በዩናይትድ ስቴትስ ኮድ በአንቀፅ (3) ንኡስ ክፍል (h) ክፍል 1365 ርዕስ 18 ስር "ከባድ የአካል ጉዳት" በሚል ተቀምጧል።

*የጦር መሳሪያ* የሚለው ቃል ትርጉም በዩናይትድ ስቴትስ ኮድ አንቀፅ (2) የመጀመሪያው ንኡስ ክፍል (g) ርዕስ 18 ክፍል 930 ስር "ለአደገኛ መሳሪያዎች" እንደተሰጠው ትርጉም።

**ማሳወቂያዎች**

የተማሪዎችን ስነ ምግባር ኮድ በመጣሱ ምክንያት በልጅዎ ላይ የምደባ ለውጥ ለማድረግ የእግድ ውሳኔ በተላለፈበት ቀን LEA ውሳኔውን ለእርስዎ ሊያሳውቅ ይገባል እንዲሁም የሂደቶች መጠበቂያ ማሳወቂያን ሊሰጥዎ ይገባል።

**<u>በዲሲፕሊን ግድፈት ምክንያት የመማሪያ ቦታ ለውጥ</u>**

**34 CFR §300.536**

የአካል ጉዳት ያለበት ልጅዎ በአካል ጉዳት ምክንያት ካለበት ቦታ መለወጥ **የመማሪያ ቦታ ለውጥ** ይባላል

1. እገዳው ከተከታታይ አስር (10) የትምህርት ቀናት የበለጠ ከሆነ፤ <u>ወይም</u>
2. ልጅዎ ተከታታይ የሆነ ቅደም ተከተል ያለው እገዳ ተጠሪ ነው ምክንያቱም፡
   ሀ. በትምህርት አመቱ ውስጥ እገዳው በድምሩ ለ10 የትምህርት ተከታታይ ቃናት ነው፤
   ለ. የልጅዎ በሃሪ ተከታታይ እገዳዎችን ካስከተለ ከዚህ በፊት በነበረው ድርጊት ውስጥ ከነበሩ ልጆች ጋር በተለየ ተመሳሳይ ነው፤ <u>እና</u>
   ሐ. በተለያዩ ተጨማሪ ሁኔታዎች ለምሳሌ የእያንዳንድ እገዳ ርዝመት፣ ልጅዎ በአጠቃላይ የታገደበት ጊዜ፣ እና የእገዳዎቹ ተቀራራቢነት

ተከታታይነት ያላቸው እገዳዎች የመማሪያ ቦታ ለውጥን በእያንዳንዱ ጉዳይ መሰረት በ LEA ይወሰናል እና፣ ከተገዳደሩት፣ በአኪያሄድ እና የፍርድ ቤት ስልጣን ስር ክለሳ የሚደረግበት ነው።፡

***የመማሪያ ቦታ ውሳኔ***

**34 CFR §300.531**

ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም ቡድን  (individualized education program (IEP) Team) ጊዚያዊ አማራጭ የትምህርት መማሪያዎች ለተባረሩ የመማሪያ ለውጦች፣ እና ***በተጨማሪ ስልጣን*** እና ***ልዩ ልዩ ሁኔታዎች*** ክፍል በተባረሩ ላይ ይወስናል፡፡

***ይግባኝ***

**34 CFR §300.532**

**አጠቃለይ**

የቅሬታ አኪያሄድ ማቅረብ ይችላሉ (የቅሬታ አኪያሄድ ደምቦች የሚለውን አርእስት ይመልከቱ) በሚከተለው የማይስማሙና የቅሬታ አኪያሄድ ችሎት መጠየቅ ከፈለጉ፡

1. በእነዚህ ዲሲፒሊን አቀርቦቶች ስር ማንኛውም ውሳኔ፤ ***<u>ወይም</u>***
2. ከላይ በተገለጸው የውሳኔ መገለጫ፡፡

LEA ልጅዎን አሁን ባለበት የመመሪያ ቦታ ማቆየቱ ለልጅዎ ወይም ለሌቹ አደገኛ ነው በሎ ካመነ የችሎት አኪያሄድ ለመጠየቅ የቅሬታ አኪያሄድ (ከላይ ይመልከቱ) ሊያስገባ ይችላል

***የችሎት መኮንን ሥልጣን***

በንዑስ አርዕስት ***ገለልተኛ የችሎቶች አኪያሄድ*** ስር ያለውን የሚያሟላ የችሎት መኮንን የችሎቱን አኪያሄድ መፈጸምና ወሳኔ ማሳለፍ አለበት፡፡ የችሎት መኮንኑ የሚከተሉትን ይወሰን ይሆናል፡

1. የችሎት መኮንኑ የልጅዎ አወጋገድ በንኡስ አርእስት ***የትምርት ቤት ሰራተኛ ስልጣን*** የሚለው ስር ያለውን የሚጻረር ወይም የልጅዎ ባህሪ ልጅዎ የአካል ጉዳት እንዳለበት የሚያሳይ ነው ብሎ ካመነ የአካል ጉዳት ያለበት ልጅዎን ወደተወገደበት መማሪያ ሊመልስው ይችላል፤ ***<u>ወይም</u>***
2. ልጆዎን አሁን ባለው መማሪያ ውስጥ ማቆየት ለልጅዎ ወይም ለሌች አደጋ ያስከትላል ብሎ የችሎት መኮንኑ ከለየ ከአርባ አምስት (45) የትምህርት ቤት ቃናት ሳልበለጠ ጊዜ የአካል ጉዳት ያለበትን ልጅዎን ተገቢ ወደሆነ ጊዚያዊ አማራጭ የመማሪያ አቅርቦት እንዲሸጋገር ሊያዝ ይችላል፡፡

LEA ልጅዎን ወደዋናው/ወደቀደመው መማሪያ ውስጥ መመለሱ ለልጅዎ ወይም ለሌች አደጋ ያስከትላል ብሎ ካመነ እነዚህ የችሎት አኪያሄዶች ሊደጋገሙ ይችላሉ፡፡

ከሚከተሉት ጉዳዮች በስተቀር እርስዎ ወይም LEA እንደዚህ አይነት የአቤቱታ አኪያሄድ ችሎት ለመጠየቅ ሲያስገቡ፣ ***በአቤቱታ ድምቦች አኪያሄዶች*** እና ***ችሎቶች በአቤቱታዎች አኪያሄድ*** ላይ በሚለው ርዕስ ስር ያለውን መስፈርት የሚያሟላ ችለት በፋጠኝ መከናወን አለበት፡

1. የግዛቲቱ የትምህረት ኤጀንሲ ወይም LEA ችሎቱ በተጠየቀ **በሃያ (20)** የትምህርት ቃናት ውስጥ የተፋጠነ የችሎት አኪያሄድ ማዘጋጀት አለበት እንዲሁም ችሎቱ በተሰማ **በአስር (10)** የትምህርት ቀናት ውስጥ በውሳኔ ማጠናቀቅ አለበት፡፡
2. እርስዎና LEA ስበሰባውን ለመሰረዝ ወይም ድርድር ለመጠቀም በጽሁፍ ካልተሰማማችሁ በስተቀር፣ የአቤቱታ አኪያሄድ ማስተዋቂያውን በተቀበሉ **በሰባት (7)** የቀን መቁጠሪያ ቀናት የመፍትሄ ውጤት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡ የአቤቱታ አኪያሄዱን በተቀበሉ **በአስራ አምስት (15)** የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ሁሉቱንም የሚያረካ መልኩ መፍትሄ ካልተገኘ ችሎቱ ሊቀጥል ይችላል፡፡
3. ግዛቱ አኪያሄዱን ለማፋጠን ከጊዜ ሰሌዳው ውጪ ለሌሎች አኪያሄዶች ቀድሞ ከመሰረተው አኪያሄድ የተለዩ የአኪያሄድ ደምቦች ሊመሰረት ይችላል፤ እነዚህ ደምቦች እዚህ ሰነድ ካለው የችከሎት አኪያሄድ ደምብ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡

እርስዎ ወይም LEA  ለሌሎች የአቤቱታ ችሎቶች ወሰኔን ይግባኝ እንደሚያቀርቡት ይግባኝዎን ሊያቀርቡ ይችላሉ (**ይግባኝ** የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ)፡፡

***የአቤቱታ ጊዜ መመሪያ***

**34 CFR §300.533**

ከላይ እንደተገለጸው፣ እርስዎ ወይም የ LEA ፋይል ከቅሬታ ጋር የተያያዙ የዲሲፐሊን ጉዳዮች፣ የችሎት መኮንኑ ወሳኔ እስኪሰማ ድረስ ወይም *የትመህርት ቤት ሰራተኛ ሥልጣን* በሚለው ስር ያለው የእገዳ ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ፣ ከሁለቱ የቀደመው፣ ልጅዎ በጊዚያዊ አማራጭ የትምህርት አቅርቦት ይቆያል፡፡

## ለልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ገና ብቁ ላልሆኑ ልጆች የሚደረጉ ጥበቃዎች

**34 CFR §300.534**

### አጠቃላይ

ልጅዎ የአካል ጉዳት ላለባቸው ለሚሰጠው ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች በቁ እንደሆነ ሳይወሰን የተማሪዎችን የሥነስራት ኮድ ከተላለፈ፣ ሆኖም ግን ወደተወሰደው የሥነስራአት እርምጃዎ የዳረገው ባህሪ ከመከሰቱ በፊት LEA ልጅዎ የአካል ጉዳት እንዳለበት ዕውቀቱ ካለው (በህግ እንደተወሰነው) ልጅዎ በዚህ ማስታወቂያ ላይ የተጠቀሱት ጥበቃዎች በሙሉ ሊመለከቱት ይችላሉ፡፡

### ለሥነስርአት ጉዳዮች የዕውቀት መሰረቶች

ወደተወሰደው የሥነስራአት እርምጃዎ የዳረገው ባህሪ ከመከሰቱ በፊት LEA ልጅዎ የአካል ጉዳት ያለበት መሆኑ ዕወቀት እንዲኖረው ይጠበቅበታል:

1. ልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉት ያልዎትን ቅሬታ በጽሁፍ ለተገቢው የትምህርት ኤጀንሲ ተቆጣጣሪ ወይም አስተዳደር ሰራተኛ፣ ወይም ለልጅዎ አስተማሪ ካቀረቡ፤
2. በ IDEA ክፍል B መሰረት ለልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ብቁ የሚያድርገው ግምገማ ለልጅዎ እንዲደረግ ከጠየቁ፤ ***ወይም***
3. የልጅዎ አስተማሪ ወይም ሌላ የ LEA ሰራተኛ ልጅዎ ስለሚያሰያው ባህሪያት ለ LEA ልዩ ትምህርት ዳሬክተር ወይም ሌላ የ LEA ተቆጣጣሪ ሰራተኛ ቅሬታቸውን ገልጸው ከሆነ፡፡

### የተለየ

በሚከተሉ ሁኔታዎች LEA እንደዚህ አይነት ዕውቀት እንዲኖረው አይጠየቅም:

1. ለልጅዎ ግምገማ እንዲደረግለት ካልፈቀዱ ወይም የልዩ ትመህርት አገልግሎቶችን ከተቃወሙ፤ ***ወይም***
2. ልጅዎ ተገምግሞ በ IDEA ክፍል B መሰረት የአካል ጉዳት እንዴሌለበት ከተወሰነ፡፡

### የእውቀት መሰረት ከሌለ ተግባራዊ የሚሆኑ ሁኔታዎች

ልጅዎ ላይ የሥነስርአት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት፣ ከላይ እንደተገለጸው ***የሥነስርአት እርምጃ ለመውሰድ የዕውቀት መሰረት*** እና ***ልዩነት*** በሚለው ስር መሰረት LEA ልጅዎ የአካል ጉዳት እንዳለበት ዕውቀት ከሌለው፣ ልጅዎ በተነጻጻሪ የአካል ጉዳት የሌለባቸው ልጆች ላይ ለሚወሰደው የሥነስርአት እርምጃ ሊዳርግ ይችላል

ሆኖም ግን፣ ልጅዎ ለሥነስርአት እርምጃ በቀረበበት ወቅት ለግምገማ ጥያቄ ከቀረበ፣ ግምገማው በተፋጠነ ሁኔታ መኪያሄድ አለበት፡፡ ግምገማው እስከሚጠናቀቅ ድረስ፣ ልጅዎ በትምህርት ቤት ባለስልጣናት በተወሰነበት፣ መታገድን ወይም ያለትምህርት አገልግሎት መባረርን ሊያካትት ይችላል፣ ወሰኔ ላይ ይቆያል፡፡ ከ LEA በተገኘው ግምገማ መሰረት ልጇዎ የአካል ጉዳት እንዳለበት ከተወሰነ፣ በ IDEA ክፍል B መሰረት LEA ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶችን፣ ከላይ የተጠቀሱተን የሥነስርአት መስፈርቶች አካቶ ማቅረብ አለበት፡፡

## በህግና ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የሚደረጉ እርምጃዎችና ሪፈራል

**34 CFR §300.535**

የ IDEA ክልፍ B የሚከተሉትን አያደርግም:

1. ኤጀንሲ የአካል ጉዳት ባለባቸው ልጆች የተፈጸሙ ወንጀሎችን ለተገቢው ባለስልጣን ሪፖርት ከድረግ ማገድ፤ <u>ወይም</u>
2. የግዛቲቱ ህግና ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ተግባራዊ የሚሆነውን የፌደራልና የግዛት ህግ ሃላፊነታቸው በሚፈቅደው መሰረት አካል ጉዳት ባለባቸው ልፈጆች ለተፈጸሙ ወንጀሎች ህጉ የሚፈቅደውን ተግባራዊ እንዳያደርጉ መከላከል

   *መዛግብትን ማስተላለፍ*

LEA የአካል ጉዳት ባለበት ልጅ የተፈጸመን ወንጀል ሪፖርት ካደረገ፣ የ LEA:

1. የልጁ ልዩ ትምህርት እና የስነስርአት መዝገቦች ኤጀንሲው ሪፖርት ላደረገለት ባለስልጣን ግንዘቤ መቅረቡን ማረጋገጥ አለበት፤ <u>እና</u>
2. የልጁ ልዩ ትምህርት እና የስነስርአት መዝገቦች ቅጂ የቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና ግላዊነት አዋጅ (Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)) እስከሚፈቅደው ድረስ ብቻ ሊያስተላለፍ ይችላሉ፡፡

## በወላጆች ብቻ ልጆችን በህዝብ ገንዘብ
## ወደግል ትምህርት ቤቶች የማስገቢያ መስፈርቶች

**አጠቃላይ**

**34 CFR §300.148 እና 5E DCMR §3018.5**

LEA ለልጅዎ FAPE ቢያቀርብሎትም በራስዎ ምርጫ ልጅዎን በግል ትምህርት ቤት ወይም ተቋም ማስተማር ከመረጡ፣ የ IDEA ክፍል B የአካል ጉዳት ያለበትን የልጅዎን የግል ትምህርት ቤት ወይም ተቋም፣ የትምህርት ክፍያን፣ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ጨምሮ LEA እንዲከፍል አይጠይቅም፡፡ ሆኖም ግን DCPS (በኮሎምቢያ አውራጃ ውስጥ ብቸኛው ሰነምድራዊ LEA እንደመሆኑ መጠን) በ CFR §§300.131 እስከ 300.144. መሰረት በወላጆቻቸው አማካኝነት በግል ትምህርት ቤት የሚማሩ ልጆችን በተመለከተ በክፍል B በተገለጸው መሰረት ልጅዎን ፍላጎታቸው የተሟላላቸው ህዝቦች ውስጥ መካተት አለበት፡፡

**የግል ትምህርት ቤት ክፍያ ተመላሽ**

ልጅዎ በ LEA ስልጣን የተለየ ትምህርትና ተዛማጅ አግልግሎቶች አቅርቦት የሚያገኝ ከሆነና ያለ LEA ስምምነት ወይም ፈቃድ ልጅዎን በግል ትምህርት ቤት፣አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማስተማር ከመረጡና ፍርድ ቤት ወይም የችሎት መኮንኑ LEA ትምህርት ከመጀመሩ በፊት በተገቢው ጊዜ ለልጅዎ FAPE አለማቅረቡንና በግል ተቋም ውስጥ ማስተማሩ ተገቢ መሆኑን ካመነ ፍርድ ቤቱ ወይም የችሎት መኮንኑ ኤጀንሲው የመማሪያውን ክፍያ ተመላሽ እንዲያደርግሎት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የግል ተቋሙ ምንም እንኳ በ OSSE እና LEA በሚቀርበው ትምህርት ላይ ተግባራዊ የሚሆነውን የግዛቲቱን መስፈርቶች የሚያሟላ ባይሆንም ፍርድ ቤቱ ወይም የችሎት መኮንኑ ተገቢ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ፡፡

**ገደብ በተመላሽ ክፍያ ላይ**

ከፍ ብሎ ባለው አንቀጽ ላይ የተገለጸው የክፍያ ተመላሽ ሊቀነስ ወይም ላይከፈል ይችላል:

- ልጅን ከህዝብ ትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ በፊት በቅርቡ እርሶ የተከፋሉበት የ IEP ስብሰባ ላይ ለልጅዎ የ FAPE ለማቅረብ በ LEA የቀረበውን ሃሳብ አለመቀበልዎን ለ IEP ካላሳወቁ፣ እንዲሁም ያልዎትን ቅሬታና ልጅዎን በህዝብ ገንዘብ የግል ትምህርት ቤት ማስተማር እነዳሰቡ የሚገልጽ አርፈተ ነገር ካላቀረቡ፤
- ልጅዎን ከሕዝብ ትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ ቢያንስ ከአስር (10) የስራ ቀናት (ማንኛውንም በስራ ቀን የሚውል በዓልን ጨምሮ) በፊት ሰለመረጃው ለ LEA የጽሁፍ ማስታወቂያ ካልሰጡ፤
- ልጅዎን ከሕዝብ ትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ በፊት LEA ልጅዎን መገምገም እንደሚፈል በጽህፍ ቢያሳውቅዎትም (ግምገማው ተገቢ እና ምክንያታዊ የሆነበትን ዐርፍተ ነገር ጨምሮ) ልጅዎን ለግምገማው ካላቀረቡ፤ ወይም
- ፍርድ ቤት የእርሶ እርምጃ ተገቢ ሰላለመሆኑ ሲያውቅ፡፡

ሆኖም ግን፣ የተመላሽ ክፍያ:

- የሚከተሉት ምክንያቶች ካሉ ማስታወቂያ ማቅረብ ባለመቻልዎ ምክንያት ክፍያው ሊቀንስ ወይም ሊከለከል አይገባም:

  ሀ. ወላጆች ማንብና መጻፍ የማይችሉ ከሆነና እንግሊዘኛ መጻፍ የማይችሉ ከሆነ፤

  ለ. LEA ወይም ትምህርት ቤቱ ማስታወቂያውን ከማቅረብ ያገድዎ ከሆነ፤

  ሐ. ከላይ የተገለጸውን ማስታወቂያ የማቅረብ ሃላፊነት እንዳለብዎ የሚገልጽ ማስታወቂያ ያልደረሰዎ ከሆነ፤ ወይም

  መ. ከላይ ያሉትን መስፈርቶች ማሟላት ልጅዎ ላይ አደገኛ አካላዊ ወይም አዕምሮዊ ጉዳት ሊያስከትል የሚችልከሆነ፡፡

**ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎን በሚከተለው አድራሻ ያነጋግሩ፡-**

**የግዛት የትምህርት ቁጥጥር ጽህፈት ቤት (Office of the State Superintendent of Education)**
**የልዩ ትምህርት ክፍል (Division of Special Education)**
810 First Street, NE, 5th Floor
Washington, DC 20002
(202) 741-0273

ይህ ሰነድ በኤሌክትሮኒክ ቅጂ በሚከተለው የድር ገፅ ይገኛል፡-
http://www.osse.dc.gov